የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለባለሀብቶች የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አመሰራረት 1

የኮሚሽኑ ዓላማ 2

የኮሚሽኑ ራዕይ 2

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር 3

የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት 3

የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት 5

የፋይናንስ ምንጭ 6

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሥራ ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ.......................... 6

የኦዲቱ አላማ 6

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 7

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 7

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 7

ክፍል ሁለት 9

የኦዲት ግኝቶች 9

ሀ. በኮሚሽኑ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከባለሃብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ጥያቄ የቀረቡ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ 9

በኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመፈጸም የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን መሠረት በማድረግ መመሪያ መውጣታቸውና መተግበራቸውን በተመለከተ፤ 9

የኢንቨስትመንት ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት ባለሀብቶች የፕሮጀክቱን አዋጭነት ጥናት (feasibility study) እንዲያቀርቡ መደረጉንና ፕሮጀክቶች ያለቸው የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይል መገምገሙን በተመለከተ፤ 14

ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጓቸውን ዕቃዎች ዝርዝር በቅድሚያ በማቅረብ ማስፈቀዳቸውንና የሚመለከተው

አካልም ለፕሮጀክቱ ያላቸውን አግባብነት ማረጋገጡን በተመለከተ፤ 17
ባለሀብቱ መንግሥት በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ተጠቃሚ
ለመሆን አስቀድሞ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርብ መደረጉን በተመለከተ፤ 23
ኮሚሽኑ ደንብ ቁጥር 270/2005 ባለሀብቱ ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት
ወይም ነባር ድርጅት ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈለጉ የካፒታልና
የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ፍቃድ መስጠቱን በተመለከተ 25
ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚያስገባቸው የሚፈቀዱ የመለዋወጫ
ዕቃዎች ደንብ 270/2005 መሠረት ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፤ 29
ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጪ እንዲያስገባቸው የሚፈቀዱ
ተሽከርካሪዎች መመሪያውን መሰረት ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፤ 32

ለ. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 35

ኮሚሽኑ ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጓቸውን ዕቃዎች
ዝርዝር በቅድሚያ በማቅረብ እንዲያስፈቅዱ ማድረጉን በተመለከተ፤ 39
የነባር ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመፍቀድ አስቀድሞ የበፊት
ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት አፈፃፀማቸው ውጤታማነት መረጋገጡን በተመለከተ፤....... 40
ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የወሰዱ ባለሀብቶች ማበረታቻዎችን ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን
ለማረጋገጥ ያለውን የክትትል ሥርዓትና ስለኢንቨስትመንታቸው የአፈፃፀም ሂደት በየሦስት ወሩ
ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤ 43
የተሰጡ ባለሀብቱ የተሰጠውን ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ
ውጪ አውሎ ሲገኝ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሰርዙንና ከተሰረዘበት
ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ መደረጉን በተመለከተ፤ 46
ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርና
በማበረታቻ አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን 50
ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ ውይይት መኖሩን በተመለከተ፤ 50

ሐ. ኮሚሽኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ
አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤ 51

ክፍል ሦስት 53
መደመደሚያ 53

ክፍል አራት
የማሻሻያ ሐሳቦች 57

አባሪ 1
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሥራ ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ

አባሪ 2
የመመዘኛ መስፈርቶች

ክፍል አንድ

መግቢያ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አመሰራረት

1. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ስያሜ ግንቦት 17 ቀን 1984 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 15/1984 መሰረት የተቋቋመ ሲሆን፤ በ1988 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለስልጣን፤ በ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤ በ1998 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በሚሉ ስያሜዎች ሲጠራ ቆይቶ ነሀሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 313/2006 የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተብሎ ተቋቁሟል፡፡ ተጠሪነቱን በተመለከተ እስከ 1994 ዓ.ም. ድረስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ተቋቁሞ ለነበረው የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ፤ በመቀጠልም ለቀድሞ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር (ለአሁኑ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር) የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

2. በኢንዱስትሪ ፖሊሲው መሠረት የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የግብርናውን ቦታ በመረከብ የመሪነቱን ሚና እንዲጫወት ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አኳያ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ዘርፍን በማበረታታትና በማስፋፋት የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን በማጠናከር ከንግድና አገልግሎት ዘርፎች የሚመነጨውን ሀብት ወደ አምራች የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዲውል ማድረግ ነው፡፡ በዘርፉ በሚደረጉ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ውድድርንና ስርጭቱን በማስፋፋት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ እና ልማታዊ ባለሀብቱን በይበልጥ ለማበረታታት በ2004 ዓ.ም. አዲስ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም ደንብ ቁጥር 270/2005 ይህንን ደንብ ለማሻሻል በድጋሚ ደንብ ቁጥር 213/2006 ወጥተው ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛሉ፡፡

3. በዚሁ መሠረት እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በዜግነታቸው ኢትዮጵያን ላልሆኑና ከኢትዮጵያን ጋር በጋራ ለመሥራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከታክስ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻው ከኮሚሽኑ በተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ መሠረት እየተፈቀደ የነበረና ከ2006 ዓ.ም. ጀምሮ ለማምረቻና ለኮንስትራክሽን ዕቃዎች በኮሚሽኑ እየተፈቀደ ሲሆን የሆቴሎችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ግን

እስከ የካቲት 2007 ዓ.ም. ድረስ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በሁሉም ክልሎች እስከ 2007 ዓ.ም. መጨረሻ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻው ክልሎቹ በሚጽፉት የድጋፍ ድብዳቤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እየተፈቀደ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ክልሎች እራሳቸው እንዲፈቅዱ ሥራው የወረደ ሲሆን የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻን አስመልክቶ ለማምረቻ መሣሪያዎች፣ ለግብርና፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት መስኮች፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማሠራጨት፣ ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት፣ ለሕንፃ ግንባታ ሪል እስቴት፣ ለትምህርትና ሥልጠና፣ ለጤና አገልግሎት፣ ለአርክቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ ለቴክኒክ ምርመራና ትንተና፣ ለአሳታሚነት ሥራ፣ ተሽከርካሪን የማይጨምር የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ፣ ለገቢ ንግድ /ቡታ ጋዝ ወይም ቢትመን ማስመጣት/፣ ለውጪ ንግድና ለጅምላ ንግድ ለሚሰማሩ ፕሮጀክቶች ከ2 ዓመት እስከ 15 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ የሚሰጥ ሲሆን ማንኛውም ባለሀብት ቢያንስ 80 በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ በኢንቨስትመንት አዋጅ በማስፈጸሚያ ደንብ ላይ ከተፈቀደለት ማበረታቻ በተጨማሪ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡

<u>የኮሚሽኑ ዓላማ</u>

4. በአገራችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እንዲመጣ ምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢ እንዲፈጠር በማድረግ፤ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በማስተዋወቅና ለኢንቨስተሮች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፡ ነው፡፡

<u>የኮሚሽኑ ራዕይ</u>

5. በ2015 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በአፍሪካ ግንባር ቀደም የኢንቨስትመንት መዳረሻ ከሆኑ አስር (10) አገሮች አንዷ ሆና ማየት፡፡

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

6. የኮሚሽኑን ሥራዎች በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠረው የሥራ አመራር ቦርድ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም የመንግሥት ኃላፊ በምክትል ሰብሳቢነት፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ የመንግሥት ኃላፊዎች በአባልነት እንዲሁም ኮሚሽኑ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-
   - የአዋጅ ቁጥር 769/2004 አፈፃፀምና የኮሚሽኑን ስራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፤
   - ከአዋጅ ቁጥር 769/2004 አፈፃፀም ጋር ተያይዘው የሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
   - እንዳስፈላጊነቱ አዋጅ ቁጥር 769/2004 እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦች እንዲሻሻሉ ሀሳብ ያቀርባል፤
   - አዋጅ ቁጥር 769/2004 እና በአዋጁ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤
   - የኮሚሽኑ ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ባለሀብቶች በሚያቀርቡት ይግባኝ ላይ ይወስናል፤
   - አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በስራ ላይ ባለው ደንብ መሰረት ከሚፈቀደው በተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፈቀድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
   - አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ብቻ የተከለሉ የስራ መስኮች ለውጭ ባለሀብት ክፍት እንዲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፈቀድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
   - እንዳስፈላጊነቱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣ ሰብሳቢዎቻቸውንና አባላቱን ይሰይማል፡፡

የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት

7. ኮሚሽኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 769/2004 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-

- የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን በተመለከተ በማዕከልነት በማገልገል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ያበረታታል፣ ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፤
- ምቹና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት አካባቢ እንዲኖር ለማድረግ የሚወሰዱ የፖሊሲና የአፈፃፀም ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የውጭ ኢንቨስትመንቶች ሊመጡ ከሚችልባቸው አገሮች ጋር አገሪቱ የምታደርጋቸውን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ጥበቃ ስምምነቶች ይደራደራል፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድም ይፈርማል፤
- ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት እንዲሁም የአገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚረዱ ጽሁፎችን እና ፊልሞችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ዓውደ ርዕዮችን፣ ዓውደ ጥናቶችንና ሴሚናሮችን እንደአስፈላጊነቱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያካሂዳል፤ በተዘጋጁ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፤ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤
- ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በባለሀብቶች፣ በመንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ በክልል መንግስታትና በሌሎች ኢንቨሰትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤
- ማናቸውንም ኢኒቨስትመንት ነክ መረጃዎች ይሰበስባል፤ ያጠናቅራል፤ወቅታዊ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤
- ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ዕድል መግለጫዎችን በማዘጋጀት ያስተዋውቃል፣ ሲጠየቅም በቅንጅት ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ተሳታፊዎችን የማገናኘት አገልግሎት ይሰጣል፤
- በተሰጠው የስልጣን ክልል መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ እንዲሁም የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን የኢንቨስትመንት ካፒታል ይመዘግባል፤
- ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶች ይመዘግባል፤
- የውጭ ኢንተርፕራይዝ የሀብት መዋጮ ሳያደርግ ከወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር የሚያደርገውን የትብብር ስምምነት ይመዘግባል፤
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

- ለባለሀብቶች የመረጃ፣ የምክር እና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ እንዲሁም የግብዓት ትስስር እንዲኖር መረጃ የማቅረብ ድጋፍ ይሰጣል፤
- የድኅረ-ኢንቨስትመንት የድጋፍና ክትትል ሥራን ለዚህ ዓላማ ከተቋቋሙ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
- የክልል ኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶችን ለማጠናከር የሚረዱ የምክርና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የጋራ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤
- ባለሀብቶች በአዋጅ ቁጥር 769/2004 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤
- አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤
- የኢንቨስትመንት ቦርዱን መመሪያዎችንና ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ በሚመለከታቸው ሌሎች አካላትም መተግበራቸውን ይከታተላል፤
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

<u>የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት</u>

8. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተዳድር አንድ ዋና ዳይሬክተርና ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ያሉት ሲሆን በስሩ የህዝብ ግንኙነት፣ የጥናትና እቅድ፣ የኦዲትና የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም የቅሬታ ማስተናገጃና የስነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት በተጨማሪም በምክትል ዳይሬክቶሬቶቹ ሥር ሁለት የሥራ ዘርፎች ያሉት ሲሆን እነሱም የኮርፖሬት አገልግሎትና የኢንቨስትመንት ኦፕሬሽን ዘርፎች ናቸው፡፡ የኮርፖሬት አገልግሎት የሥራ ዘርፍ በሥሩ የአሰራር ማሻሻያና የሰው ሀብት እና የፋይናንስና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ያሉት ሲሆን በኢንቨስትመንት ኦፕሬሽን ዘርፍ ሥር ደግሞ የኢንቨስትመንት ህግ ጉዳዮች፣ የክልል ኢንቨስትመንት ጉዳዮች፣ የመረጃና የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን፣ የፈቃድና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት፣ የኢንቨስትምንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ እና የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ ዳሬክቶሬት አሉት ከነዚህ የሥራ ክፍሎች ውስጥ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ እና

የጉሙሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ ዳሬክቶሬት በቀጥታ ከኦዲት ሥራው ጋር የሚገናኙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ኮሚሽኑ በመዋቅር የተፈቀደለት 364 ሠራተኛ ቢሆንም በሰኔ 2007 ዓ.ም በሥራ ላይ ያሉት ወንድ 94 እና ሴት 94 ሠራተኞች በድምሩ 188 መሆናቸው በተጨማሪም የጉሙሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ ዳይሬክቶሬት በመዋቅር የተፈቀደለት 20 ሠራተኞች ቢሆንም አሁን በሥራ ላይ ያሉት 7 ሠራተኞች ብቻ መሆናቸው እንዲሁም የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በመዋቅር የተፈቀደለት 77 ሠራተኞች ቢሆንም አሁን በሥራ ላይ ያሉት ግን 28 ብቻ መሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

9. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸዉን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገዉን የገቢ ምንጭ የሚያገኘው ከመንግሥት በሚገኝ በጀትና ከባለሀብቶች ከሚሰበሰብ ገንዘብ ሲሆን በዚሁ መሰረት በ2005 በጀት ዓመት ብር 12,515,404.64፣ በ2006 በጀት ዓመት ብር 21,106,989.27 እና በ2007 በጀት ዓመት ብር 23,301,099.38 በድምሩ ብር **56,923,493.29** ገቢ ያገኘ ሲሆን በየበጀት አመቱ ለተለያዩ ወጪዎች በ2005 ዓ.ም፣ በ2006 ዓ.ም እና በ2007 ዓ.ም በቅደም ተከተል ብር 9,619,482.32፣ ብር 15,768,206.96፣ ብር 16,658,890.71 በጠቅላላ ብር **42,046,579.99** ለተለያየ ወጪዎች አውጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሥራ ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ

10. ከኮሚሽኑ የሥራ ዘርፎች የኢንቨስትምንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ እና የጉሙሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ ዳሬክቶሬት ከኦዲቱ ጋር ተያያዥ ሆነው የተገኙ ሲሆን በእነዚህ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰሩ ስራዎች የአሰራር ሂደት መግለጫ(process description) በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ አላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸምን በተመለከተ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ላወጡ ባለሀብቶች እየተሰጠ ያለው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የወጡ አዋጅና ደንቦችን መሠረት ያደረገ መሆኑን፣ ባለሀብቶች ያገኙትን

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለተፈቀደለት አላማ ብቻ ማዋላቸውን ለማረጋገጥ ያለው የክትትል ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በመገምገም በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

12. ከላይ የተመለከተውን የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት፤ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለባለሀብቶች የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ለተከናወነው የክዋኔ ኦዲት ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል። እነሱም ፦
    1. በኮሚሽኑ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከባለሃብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ጥያቄ የቀረቡ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
    2. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፤
    3. ኮሚሽኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

    የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

13. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሦስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች 25 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተመረጡት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከዋል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው በአባሪ 2 ቀርበዋል ፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

14. ኦዲቱ የሚከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2005 በጀት ዓመት እስከ 2007 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ

የተሰራውን ሥራ ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የሚከናወነው በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ በናሙና የተመረጡ የክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች በናሙና የተመረጡ ባለሀብቶች እና የተለያዩ ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመሰብሰብና በመከለስ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና በአካል በማየት ነው፡፡

15. በዚህም መሠረት በናሙና ለተመረጡ ለ6 የክልልና በክልል ከተሞች ለሚገኙ ኢንቨስትመንት ቢሮዎች (የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ልማታዊ ባለሀብት መሳብና መደገፍ ዋና የሥራ ሂደት፣ የትግራይ ክልል ኢንቨስትመንት የሥራ ሂደት፣ ለባህርዳር በኢንዱስትሪ ልማትና ከተማ አገልግሎት መምሪያ የባ/መ/መ/ኢ. ዋና የሥራ ሂደት፣ ለአክሱም ኢንቨስትመንት የሥራ ሂደትና አዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ)፣ ለ4 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች (አቃቂ ቃሊቲ፣ መቀሌና ባህርዳር ቅርንጫፍ መ/ቤቶችና ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ግብር ከፋዮች) በመሄድና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ክፍል ሁለት

<u>የኦዲት ግኝቶች</u>

ሀ. በኮሚሽኑ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከባለሀብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ጥያቄ የቀረቡ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመፈጸም የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን <u>መሠረት በማድረግ መመሪያ መውጣቱንና መተግበሩን በተመለከተ</u>፤

16. *ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ማበረታቻን በተመለከተ የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን መሠረት በማድረግ መመሪያ ሊያወጣና ሊተገብር ይገባል እንዲሁም በተገቢው አካል ጸድቀው ሥራ ላይ የሚውሉ መመሪያዎች የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን በብቃት ለማስፈጸም ግልጽነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡*

17. *በኦዲቱ ወቅት በተከለሰ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ እንዲሁም በቃለመጠይቅ በተገኘ መረጃ በኮሚሽኑ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተጠንተው ሥራ ላይ እንዲውሉ የተደረገ መሆኑ የኮሚሽኑን ጥረት የሚያሳይ ሲሆን ነገር ግን የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር መመሪያ አለመውጣቱ፣ የካፒታል ዕቃዎችና የግንባታ ዕቃዎች በመጠን የተገደበ ህግ የሌለና ባለሀብቱ የጠየቀው ማበረታቻ በሙሉ የሚፈቀድበት ሁኔታ መኖሩ፣ በአስጎብኚነት የስራ መስክ ላይም የተሰማሩ ከቀረጥ ነፃ ያስገቡትን እቃ ሲያከራዩ ማሳወቅ ቢኖርባቸውም የማያሳውቁ መሆኑን እና በማያሳውቁ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርግ የአፈፃፀም መመሪያ አለመኖሩ፣*

18. *የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የሚያከራዩ ባለሀብቶች እቃዎችን እንዴት እና በምን ሁኔታ ማከራየት እንዳለባቸው በዝርዝር የሚገልጽ መመሪያ ያልወጣ መሆኑ፣ በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶችን ከማበረታታት አንፃር አሁን እየተሰራበት ያለው መመሪያ የባለሀብቶችን የመሬት ይዞታ ያላገናዘበ መሆኑ፣ /አነስተኛና ሰፊ የመሬት ይዞታ ያላቸውን ባለሀብቶች ተመሳሳይ የሆነ የተሽከርካሪ*

ማበረታቻ እንዲያገኙ መደረጉ በአበባ ልማት የሚሰማሩ ባለሀብት ከ10 እስከ 30 ሄክታር ለሚያለማ አንድ ፒክ አፕ መኪና የሚፈቅድ ሲሆን፣ ከ30 ሄክታር በላይም ለሚያለማ የአበባ ልማት ባለሀብት አንድ ፒክ አፕ መኪና ብቻ መፈቀዱ እና የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት የገቢ ግብር ማግኘት ካለበት ጊዜ ሲያሳልፍ /ሲያጭበረብር/ ባለሀብቱ የሚቀጣበት ደንብ ወይም መመሪያ አለመኖሩ፣

19. እንዲሁም በወጡ ደንብና መመሪያዎች ላይ ግልፅ ያልሆኑ አንቀጾች ያሉ ሲሆን በደንብ ቁጥር 270/2005 የገቢ ግብር ማበረታቻ ሠንጠረዥ ላይ ሌሎች የመሳሰሉት የሚሉ አንቀጾች መኖራቸውና / 1/3.4 የጨርቃ ጨርቅ ማጠናቀቅ ሥራዎች ሌሎች፣ 1/6.4 የወረቀት ውጤቶች ማምረትና ሌሎች፣ ሠንጠረዥ 1/3.13 የእጅ መሣሪያ ቁሳቁስና የመሳሰሉትን ማምረት …./ ሌሎችና የመሳሰሉ የሚሉት ቃላቶች በትክክል የትኞቹ የኢንቨስትመን መስኮች እንደሆኑ የማይገልጽ በመሆኑ አፈጻጸም ላይ ክፍተት መፍጠሩ ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በመጋቢት 4 2005 ዓ.ም. ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ አንቀጽ 4 ሠንጠረዥ 1 ቁጥር 8/8.8 ሌሎች የኬሚካል ውጤቶችን ብሎ (ባሩድ፣ ፈንጂ፣ የፎቶግራፍ ፊልም እና የመሳሰሉትን) ማምረት፣ አንቀጽ 4 ሠንጠረዥ 1 ቁጥር 13/13.2 የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና ምስማርን ሳይጨምር ሌሎች የብረታ ብረት ውጤቶችን (የእጅ መሣሪያ፣ ቁሳቁስ እና የመሳሰሉትን) ማም ረት …../ የሚሉ ቃላቶች ያሉና የመሳሰሉት እነማን እንደሆኑ አለመገለጹ አፈፃፀም ላይ ክፍተት መፍጠሩ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ መመሪያ ላይ አንቀጽ 6 ቁጥር 2/ሀ ላይ ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ለመፍቀድ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም የሚመለከተው ሌላ የመንግሥት አካል ለየደረጃው እንደሚያስፈልጉ ከዘረዘራቸው መሣሪያዎች በዋጋ 25% ያህሉን ከውጭ አገር ስለመግዛቱ የዋጋ ግምት ማረጋገጫ ሠነድ ያቀርባል የሚል ሲሆን 25 በመቶ በአዲስ ይሁን ወይም የበፊት ካፒታል ዕቃ አለመገለጹ በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ግልጽነት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

20. በሌላ መልኩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻን አስመልክቶ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ አንዳንድ የማይተገበሩ /የሚጣሱ/ መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

21. ለምሳሌ በኢንቨስትመንት አዋጅ 769/2004 አንቀጽ 20 ቁጥር 1 ላይ ስለፕሮጀክት አፈጻጸም ባለሀብቶች በየሦስት ወሩ የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19 ቁጥር 2/መ እና ሠ ላይ የሚጠበቅባቸውን ሪፖርት በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ካላቀረቡ፣ ፕሮጀክቱ ትግበራው በሚጠበቀው ጊዜ ካልተጠናቀቀና እንደማይጠናቀቅ ኮሚሽኑ ሲያምንበት ድርጅቱ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ይሰረዛል ቢልም ሪፖርት የማያቀርቡ ድርጅቶችና በሚጠበቅባቸው ጊዜ ወደ ትግበራ የማይገቡ ድርጅቶች የማይሰረዙ መሆናቸው እና ከኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 ውጭ ባለሀብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ከፕሮጀክታቸው ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ማለትም /ለአብነት ያህል ጆርጅ ሹ የጫማ ፋብሪካ፣ የዳሸን ፋብሪካ ኤም.ኤን.ኤስ የቤት ቁሳቁሶች፣ ቪድዮ ካሜራዎች ..../ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተፈቀደ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. በኢንቨስትመንት ደንብ 270/2005 ላይ ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የጥሬ ዕቃዎች እንዲገቡ በደንቡ ላይ ያልተገለጸ ቢሆንም ቦርዱ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስም ሺንዞ ኦሬይንት /ዶንግፋንግ/ ከተባለ ድርጅት ጋር ለሚያመርተው ዕቃ የጥሬ ዕቃ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ውል መዋዋሉና ጥሬ ዕቃዎቹ በገንዘብ ሚኒስቴር ፍቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ መደረጉ፣

23. ስለጉዳዩ በገቢዎችና ጉምሩክ የመንግሥት የተሰጡ መብቶች ማስፈፀሚያ የሥራ ሂደት አስተባባሪ ሲገልጹ የአፈፃፀም መመሪያ አለመኖሩ ሥራ ላይ ክፍተት እየተፈጠረ መሆኑና የግንባታ ዕቃ ላይ ባለሀብቶች ባቀረቡት ቢል ኦፍ ኳንቲቲ ስለሚጸድቅ ባለሀብቶች በተለይ ብረቶች ያለአግባብ ፕሮጀክታቸው ከሚፈልገው በላይ እያስገቡ በመሆኑ ለባለኮከብ ሆቴሎች ስታንዳርድ መውጣት እንዳለበት፣ ካፒታል ዕቃንም አስመልክቶ ቴክኖሎጂ እያደገ ስለመጣ ዝርዝር መመሪያ ማውጣት አስቸጋሪ መሆኑን ነገር ግን ማስፋፊያ በሚል አላግባብ እየገቡ መሆናቸውና ቁጥጥር ባለመኖሩ ከቀረጥ ነፃ የገባው እና ሥራ ላይ ያለው የተለያየ

መሆኑን ገልጸው ነገር ግን ቢያንስ ዋና ዋና የሚባሉ ዕቃዎች ላይ ዝርዝር መመሪያ ማውጣት ቢቻል ተገቢ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

24. በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጉዳዮ የሚመለከታቸው ኃላፊ ተጠይቀው የአምራች ድርጅቶች ዕቃ ብዙ እንደሆነና የካፒታል ዕቃን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ ማውጣት የማይቻልና እነሱም በኢንተርኔት ፈልገው የሚፈቅዱ መሆኑን፣ ለግሪን ሀውስና በሆቴል ላይ ጥቃቅን ዕቃዎችንም ስለሚይዙ ዝርዝር መመሪያ መውጣቱን የግንባታ ዕቃንም አስመልክቶ ስታንዳርድ ባይወጣም በመንግሥት አካላት ቢል ኦፍኳንቲቲ እንዲጸድቁ ማድረግ እንደሚቻል ነገር ግን የአዲስ አበባ መስተዳድር እያጸደቀ አለመሆኑንና በአሠራር ላይም መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡

25. በመሆኑም የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማበረታቻን አስመልክቶ የአፈጻጸም መመሪያዎቹ ተገቢ ዝርዝሮቹን ባካተተ መልኩ ያለመውጣታቸውና እንዲሁም እነዚህ መመሪያዎች በባለሙያዎች ተጠንተው ሊወጡ የሚችሉና እንደቴክኖሎጂው መለወዋወጥም በየጊዜው ክለሳ ሊደረግላቸው የሚችል በመሆኑ የመመሪያዎቹ አለመኖር ባለሀብቱ ዕቃዎችን ያለአግባብ እንዲያስገቡ የአሠራር ክፍተት የፈጠረ ሲሆን አገሪቱ ያለአግባብ የቀረጥ ነጻ መብት በመስጠት አላግባብ የቀረጥ ገቢ እንድታጣ በማድረግ ጉዳት እያስከተለ በመሆኑ መመሪያዎች አለመውጣታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

26. ኮሚሽኑ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጠው መልስ የግንባታ ዕቃ በደንብ ቁጥር 270/2005 ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 312/2006 መሰረት የግንባታ ዕቃ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣ በኋላ ማስገባት የማይፈቀድ መሆኑን፣ እንዲሁም የተሻለ የሥራ ዕድል ለሚፈጥሩና ከፍ ያለ ካፒታል ለሚያወጡ የአገልግሎት ዘርፎች የንግድ ፈቃድ ካወጡበት ጊዜ አንስቶ እስከ 5 ዓመት ድረስ ብቻ የካፒታል ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደንገጉን በተጨማሪም የግብርና እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ላይ ለሥራ ዕድል እና ሥራ ላይ ላዋለ ባለሀብት የካፒታል ዕቃ ዝቅተኛ መስፈርቱን ካሟላ ተጠቃሚ መሆን የሚችል መሆኑና ከዚህ በላይ መገደቡ የማኑፋክቸሪንግ እና ከፍተኛ ትራንስፎርሜሽን የሚጠበቅበትን የግብርና ዘርፎች እንዲቀጭጩ ከማድረጉም በላይ ማበረታቻ ከሚሰጡ የኢንቨስትመንት ተወዳዳሪ አገሮች ጋር መወዳደር እንዳይቻል እንደሚያደርግ

በተጨማሪም ደንቡ ላይ ለአፈጻጸም ግልጽ ያልሆኑ ሌሎች የመሳሰሉት የሚሉ ቃላቶች መካተታቸውን በተመለከተ ሁሉንም የሥራ መስኮች መዘርዘር ስለማይቻል ከኢዚክ ኮድ በማየት እንዲስተናገዱ የሚደረግ መሆኑን እንዲሁም ነፃ የገቢ ግብር ማበረታቻ ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ ተጠቃሚ ለሚሆኑ ባለሀብቶች እንዲቀጡ የሚያስችል የወጣ መመሪያና ደንብን አስመልክቶ በታክስ ህጉ የተሸፈነ መሆኑንና ዋናውን ከነወለዱ እና ከነመቀጫው እንደሚከፈል እንዲሁም በየሦስት ወሩ ሪፖርት የማያቀርቡ ባለሀብቶችን በተመለከተ የኢንቨስትመንት ፍቃዳቸውን መሰረዙ አገር እንደሚጎዳ ተገልጿል፡፡

27. ይሁን እንጂ የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻን አስመልክቶ በታክስ ህጉ ላይ ነፃ የገቢ ግብርን እንደሚያካትት ያልተገለጸና በታክስ ህጉም መሰረት እየተሰራበት አለመሆኑን የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት ማረጋገጥ የቻለ ሲሆን ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚገቡ ዕቃዎችን አስመልክቶ በሪፖርቱ የተገለጸው በመጠን መገደብ እንዳለበት ሲሆን በኮሚሽኑ የተገለጹት ግን በመጠን ሳይሆን በጊዜ መገደቡን የሚያሳይ በመሆኑ እንዲሁም በደንብ ቁጥር 312/2006 በቁጥር 5/ሀ ላይ የካፒታልና የግብርና ዕቃዎች በተመለከተ ማንኛውም ባለሀብት ዝቅተኛውን መመዘኛ ካሟላ በማናቸውም ጊዜ ማስገባት እንደሚችል የተገለጸ ሲሆን በመጠን ያለመገደቡና የቀረጥ ነፃ ማበረታቻው ለአገሪቱ የሚያስገኘው ጥቅም እና ማበረታቻውን የሚያገኙ ባለሀብቶች ለሀገሪቷ እየሰጡ ያሉትን ፋይዳ በማይገመግምበት ሁኔታ ባለሀብቱ የጠየቀውን ሁሉ መስጠቱ የቀረጥ ነጻ ማበረታቻውን ዓላማ የተዛባ የሚያደርገውና በዚህ ሪፖርት ላይ ለማሳያነት እንደተገለጹት ባለሀብቶች ዕቃዎችን አስገብተው ለሽያጭ ለመሳሰሉት እንዲያውሉም በር የሚከፍት በመሆኑ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

28. ለአፈጻጸም ግልጽ ያልሆኑ ቃላቶችንም በተመለከተ በተለይ በአሁኑ ወቅት ክልሎችም የኢንቨስትመንት ቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን ፍቃድ እንዲሰጡ የተደረገና የኦዲት ቡድኑ ለኦዲት ሥራው በተንቀሳቀሰበት ወቅት ከላይ የተገለጹት ቃላቶች/ሌሎች የመሳሰሉት የሚሉት/ ለአሰራር ችግር እንደሚፈጥሩ በሥራው ላይ ያሉ ኃላፊዎች የገለጹ በመሆኑ በግልጽ ቢቀመጥ ለአሰራር አመቺ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከላይ በሪፖርቱ እንደተገለጸው በየሦስት ወሩ ሪፖርት የማያቀርቡ ብቻ ሳይሆን በጊዜው ወደ ትግበራ የማይገቡ ፕሮጀክቶችንም ጭምር ፍቃዳቸው

እንዳልተሰረዘ የተገለጸ ሲሆን ወደ ትግበራ የማይገቡ ፕሬጀክቶችን አስመልክቶ የተሰጠ ምላሽ የሌለ መሆኑና የወጡ ደንብና መመሪያዎች ሊተገበሩ የሚገባ ሲሆን ሪፖርት በማያቀርቡ ድርጅቶችን መሰረዙ አገር እንደሚጎዳ ከታመነበት ኮሚሽኑ ደንቡን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ እንዲሻሻል ሊያስደርግ ይገባል፡፡

የኢንቨስትመንት ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት ባለሀብቶች የፕሮጀክቱን አዋጭነት ጥናት (feasibility study) እንዲያቀርቡ መደረጉንና
<u>ፕሮጀክቶች ያለቸው የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይል መገምገሙን በተመለከተ፤</u>

29. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፍቃድ እንዲሰጠው ጥያቄውን ለኮሚሽኑ የሚያቀርብ ባለሀብት የፕሮጀክቱን አዋጭነት ጥናት (feasibility study) እንዲያቀርብ ሊያደርግና ለባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከመስጠቱ በፊት ባለሀብቱ ያለው የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይል ሊገመገም ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ሆነ በናሙና ከታዩት የትግራይ፣ የአማራና የኦሮሚያ ክልል የአዲስ አበባ፣ የአክሱምና ባህርዳር ከተማ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲያወጡ የአዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡ አይደረግም፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍቃድም ሆነ የቀረጥ ማበረታቻውን ለመስጠት የባለሀብቶቹ የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይል እንደማይገመገም በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

31. በዚህም ምክንያት በሚፈለገው ጊዜ ወደ ትግበራ የማይገቡና ወይም አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን በናሙና ከታዩት ድርጅቶች በባህርዳር ከተማ በአበባ ምርት ላይ የተሰማራ ኢትዮ አግሪ ሴፍት የተባለ ድርጅት መጀመሪያ ወደ ስራው ሲገባ የአዋጭነት ጥናት በድርጅቱ ያልተጠናና በመንግስት ቦታው ተከልሎ ለአበባ ምርት አዋጭ ነው ተብሎ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ነገር ግን ወደ ስራው ሲገቡ ቦታው የከርሰ ምድር ውሃ ስለሌለው ከጣና ሀይቅ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ውሃ በፓምፕ እየሳቡ እየተጠቀሙ መሆኑንና በዚህም ምክንያት ላልተፈለገ ወጪ እንደተዳረጉና ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ ለመግባት ለ7 አመት መዘግየቱ ታውቋል፡፡ ድርጅቱ የሚያመርተውን የአበባ ምርት ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ የባህዳር ኤርፖርት አበባውን ለማቆየት የሚያስችል ፍሪጅ ባለመኖሩና ወደ አዲስ አበባ

መጥቶ እስኪጫን ድረስ የአበባውን ጥራት የሚቀንስ በመሆኑ ከአለም አቀፉ ገበያ ጋር ለመወዳደር እንደተቸገሩ የድርጅቱ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

32. በተመሳሰይ መልኩ አሽራፍ የተባለ የሥጋ ማቀነባበሪያ ድርጅት ፈቃድ ሲያወጣ የአዋጭነት ጥናት ያላቀረበ መሆኑና በዚህም ምክንያት ድርጅቱ ሲቋቋም ለሥራው የሚያስፈልገው ግብዓት በቅርብ ስለመገኘቱ ሳይጠና በመቋቋሙ ለፋብሪካው የሚያስፈልገውን ግብዓት ከባህርዳር 800 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከቦረና ከብት ገዝተው የሚያመጡ በመሆኑ ምክንያት ለኪሳራ መዳረጋቸው ገልጸዋል፡፡ የሥጋ ማቀነባበሪያው የተመሰረተው በ1996 ዓ.ም. ሲሆን ከተመሰረተ እስካሁን በ2003 ዓ.ም. ብቻ ወደ ውጭ ያመረተውን ምርት የላከ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ሙሉ ለሙሉ ሥራውን ማቋረጡን በኦዲቱ ወቅት የድርጅቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኮሚሽኑ በ2006 ዓ.ም. በተጠና ጥናት ለውጭ ገበያ ምርታቸውን ለማቅረብ የተሳተፉ ባለሀብቶቹ ተገቢውን ቅድመ-ጥናት ሳያደርጉና አቅማቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ የሚጠይቁትን የመሬት መጠን በአግባቡ ባለመወሰናቸው የተረከቡትን መሬት አገልግሎት ላይ እንዳላዋሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. እንዲሁም ባለሀብቶች ያላቸው የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይል ባለመገመገሙ በባህርዳር ከተማ ኢንቨስትመንት ቢሮ ፍቃድ ከወሰዱ ባለሀብቶች ብዙ ቢሆኑም ትግበራ ላይ ያሉት ትንሽ መሆናቸው በተመሳሳይ በትግራይ ክልል የአብዛኛው ባለሀብት አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

34. በኮሚሽኑ በ2006 ዓ.ም. በተጠና ጥናት በእርሻ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች በቂ ካፒታል ይዞ አለመግባት እና በዚህም የተነሳ በሚታየው ደካማ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተረከቡትን መሬት በአግባቡ አለመጠቀማቸውና ውጤታማነታቸው በዙሪያው ከሚገኙ አርሶአደሮች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ መሆኑ ተገልጿል። ኩባንያዎቹም በአብዛኛው በቂ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ባለው የሰው ሀይል አለመመራታቸው፣ ለሰራተኞች ምቹ የስራ አካባቢ የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚካሄዱ ልማቶች አዝጋሚና ጥራት የጎደላቸው መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. በተጨማሪም በጋምቤላ ክልል ባለሃብቶች በሚጠበቀው ደረጃ የፋይናንስ አቅም ተደራጅተው ባለመሰማራታቸው በዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ክፍተቶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ ለምሳሌ ትራክተሮች እና ሌሎች የእርሻ

መሳሪያዎችን በበቂ ደረጃ አለመሟላት እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለመጠቀም ችግር እንዳለ ከጋምቤላ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚሁ ክልል ካራቱሪና ሩቺ የተባሉ የህንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኢንቨስትመን ፍቃዳቸውን ያገኙ ሲሆን አቅማቸውን ባላገናዘበ መንገድ በተከታታይ 100,000ና 25,000 ሄክታር መሬት የተረከቡና የታክስ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ከ2003-2005 ዓ.ም. ብር 157,108,478 እና 16,293,518 ተጠቃሚ የሆኑ ቢሆንም በአፈፃፀማቸው ግን እጅግ በጣም አነስተኛና ሩቺ የተባለው ድርጅት ከአራት ዓመት ቆይታ በኋላ በ2006 ዓ.ም. ውጤታማ ባለመሆኑ የመሬት ይቀነስልኝ በሚል ጥያቄ ለማቅረብ መቻሉንና ካራቱሪም ኢንቨስትመንት ፍቃዱ በ2007 ዓ.ም. በኮሚሽኑ መሰረዙን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኮሚሽኑ ሥራ ፕሮጀክቶች የሰው ኃይል ከውጭም ይሁን ከአገር ውስጥ እንዲቀጥሩ መፍቀድ መሆኑን እና የፋይናንስ አቅማቸውንም በተመለከተ ዝቅተኛውን መመዘኛ ማለትም በደንቡ መሠረት /150,000 እና 200,000 USD/ እንደሚያዩና ደንቡም የሚያዘው ይኼንኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኢንቨስተሮች ተገቢው አቅም እንኳን ባይኖራቸው ምርታቸውን ከፍ አድርገው አቅም እንዲኖራቸው ከውጭ ዕቃ እንዲያስገቡ እንደሚያደርጉ የገለጹ ሲሆን በኢንቨስትመንት የሚሳተፉ ባለሀብቶች ማቅረብ የሚገባቸውን ጥናትን በተመለከተ ጥናት መቅረቡ አስፈላጊ እንደሆነ አምነው ነገር ግን ባለሀብቶቹ ጥናት ያቅርቡ ቢባል እንኳን ከዚህ በፊት ተሞክሮ በአሠራር ላይ ክፍተት እንደፈጠረና ለአንዱ ባለሀብት የተሰራው ጥናት ኮፒ እየተደረገና እየተቀያየረ ስለሚቀርብ ውጤታማ ባለመሆኑ እንደተተወ ገልጸዋል፡፡

37. ይሁን እንጂ የስራ ኃላፊው አስተያየት በአሠራር ላይ የታየውን ክፍተት ባለሀብቶች ኢንቨስት ስለሚያደርጉበት የሥራ ዘርፍን አስመልክቶ የአዋጭነት ጥናት አለማቅረባቸው እና የኢንቨስተሮቹ የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይልን አስመልክቶ በኮሚሽኑ ተገቢው ግምገማ አለመደረጉ በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረገ ሲሆን አገሪቱም ያላትን ውሱን ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን አድርጓል፡፡

38. በኮሚሽኑ ኦዲት ሪፖርቱ ላይ በተሰጠው መልስ የኢንቨስተሮቹ የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይልን በኮሚሽኑ መገምገሙን አስመልክቶ ኮሚሽኑ የውጭ ባለሀብቶችን አቅም እና የኢንቨስትመንት ምንጭ የኋላ ታሪክ ጥናት ማጥናት እንዳለበት በማመን በአዲሱ አደረጃጀት ውስጥ በምክትል ኮሚሽነር በሚመራው የፖሊሲ ጥናትና አፈጻጸም ዘርፍ ሥራ በዳይሬክቶሬት ደረጃ የተደራጀ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በኮሚሽኑ የአዋጭነት ጥናት ባለሀብቶች እንዲያቀርቡ አለመደረጉን አስመልክቶ ሁሉም ባለሀብቶች የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡ ማድረግ ጥናቶች ከመቶ ሺዎች እስከ ሚሊዮኖች ብር የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን ለማቅረብ ፈቃደኛ የማይሆኑ ባለሃብቶች በርካታ መሆናቸውን፣ የውጭ ባለሃብቶችን ጥናቱን እንዲያቀርቡ ከተገደዱ ሌላ አገር ሄደው ኢንቨስት የማድረግ ምርጫ ስላላቸው አገሪቷ ልታጣቸው እንደምትችል ገልጸዋል፡፡

39. ሆኖም የአዋጭነት ጥናቱ ባለሀብቶች ለሚያቀቁሙት ፕሮጀክት ቀጣይትን ከማረጋገጥ አንፃር ለባለሀብቱ የሚጠቅም በመሆኑ ስለጠቀሜታው ኮሚሽኑ ለባለሀብቶች የማስረዳት ሥራ መስራት የሚጠበቅበትና ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች ላይ የታዩ ችግሮችን ሊቀርፍ የሚያስችል እንዲሁም ባለሀብቱ ብድር እና መሬት ሲጠይቅ እንዲያቀርብ የሚደረግና እያቀረበም ያለ በመሆኑ የአዋጭነት ጥናቱ እንዲያቀርቡ አለመደረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ
<u>የሚፈልጓቸውን ዕቃዎች ለፕሮጀክቶቹ ያላቸውን አግባብነት መረጋገጡን በተመለከተ</u>፤

40. ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተጠየቁት መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና አክሰሴሪዎቻቸው ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው መሆኑን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

41. በናሙና በታዩት በትግራይ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል፣ በአዲስ አበባ፣ በአክሱምና ባህርዳር ከተሞች በሚገኙ የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው መሆናቸው ሳይረጋገጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕቃዎችና አክሰሴሪዎች መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

42. በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ባለሀብቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እንዲገቡላቸው የሚጠይቋቸው ዕቃዎችና አክሰሴሪዎቻቸው ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ ላይ ችግሮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ የካፒታል ዕቃን አስመልክቶ የአምራች ድርጅቶች ላይ በዝርዝር ባለመቀመጡ በኢንተርኔት ለማረጋገጥ የሚሞከር መሆኑንና የቀረጥ ነጻ ማበረታቻውን የሚያከናውኑ ሰራተኞች ላይም የአቅም ውስንነት መኖሩ የሚመለከታቸው ኃላፊ ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለሙያ የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ተገቢው የሙያ ስብጥር ኮሚሽኑ ያላሟላ በመሆኑ ዕቃዎችን በተመለከተ የቀረጥ ነፃ የጠየቁ ድርጅቶች ማብራሪያ እንዲሰጡበት በመጠየቅና የነሱን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የመወሰን ሁኔታ መኖሩ በኮሚሽኑ በተገኙና በተከለሱ መረጃዎች ታውቋል፡፡

43. እንዲሁም በአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ሊፈቀድ የሚገቡና የማይገቡ ዕቃዎች በግልጽ አለመለየትና አለማወቅ በተመሳሳይ መልኩ በሆቴል ዘርፍ የዕቃዎችን ምንነት በአግባቡ ለመለየት የማይችሉና ለፕሮጀክቱ አግባብ ይሁኑ አይሁኑ እርግጠኛ ሳይሆኑ /subjective/ ሆነው የሚወስኑ መሆኑ ታውቋል፡፡ በኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የጉምሩክ የቀረጥ ነፃ ጥያቄ በባለሀብቶች ሲቀርብ ዕቃዎችን በአብዛኛው ለይተው የማያውቋቸው መሆኑና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ሲፈቅድ ይለየዋል በሚል አግባብነቱ ሳያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ የሚጽፉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

44. በተመሳሳይ መልኩ በአክሱም ከተማ የኢንቨስትመንት ቢሮ በግንባታ ዕቃዎች የጉምሩክ የቀረጥ ነፃ ጥያቄዎች ላይ በህንፃ ቁጥጥር ጽ/ቤት በባለሞያ የሚረጋገጥ ቢሆንም ሌሎች እቃዎች ግን የማረጋገጫ ስርዓት የሌላቸው በመሆኑ ሳያረጋግጡ የሚያሳልፉ መሆኑን እንዲሁም በአማራ ክልል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተጠየቁት መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና ዘ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

45. በተጨማሪም በትግራይ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ በሌሎች የስራ ዘርፎችም ሆነ ለግንባታ እቃዎች ወጥ የሆነ መመሪያ ስለሌለና መጠኑ ላይ ስላልተገደበ ሙሉ በሙሉ ባለሀብቶች የተጠየቁትን የጉምሩክ የቀረጥና ነጻ ድጋፍ የሚያሳልፉ

መሆኑን የሚመለከታቸው ኃላፊ በኦዲቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም የኦዲት ቡድኑ በክልሉ በሆቴል ግንባታ የተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያቀርቧቸውን የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማበረታቻ አሰራርን አስመልክቶ ባካሄደው ግምገማ የግንባታ እቃዎች በየደረጃው ምን ያህል መግባት እንዳለባቸው በመጠን የተቀመጠ የአፈጻጸም መመሪያ ባለመኖሩና ባለሀብቱ ባቀረበው ቢል ኦፍ ኳንቲቲ የሚፈቀድ በመሆኑም በክልሉ ወደ 69 የሚሆኑ ባለሀብቶች በ11 ከተሞች በአነስተኛ ከተሞች ማለትም /በእንትጮ፣ በውቅሮ፣ በአጽቢና በአጉላዕ..../ ባለኮከብ ሆቴሎች እንደሚገነቡ በመግለጽ የጉምሩክ ከቀረጥ ነፃ ጥያቄዎችን ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም. ግንባታው ከሚፈለገው ብረት በላይ ቢል ኦፍ ኳንቲቲ በማሰራት በአጠቃላይ ብር 311,841,873.87 ያለአግባብ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ መሆናቸውና ከ69 ውስጥ 7ቱ አድራሻቸው አለመገኘቱ፣ 16ቱ ግንባታ ጀምረው ያቆሙና 2ቱ ምንም ያልጀመሩ መሆኑን ግንባታቸውን የጨረሱትም ቢሆን ግንባታው ላይ ከተጠቀሙት ብረት በላይ ማስገባታቸውን ከገቢዎችና ጉምሩክ የመቀሌ ቅርንጫፍ በኦዲት ወቅት በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. በሌላ መልኩ በተለይ ሆቴሎችን እንገነባለን በማለት ከፍተኛ መጠን ያላቸው ብረቶችን ከጉምሩክ የቀረጥ ነፃ መብት በመጠቀም ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡ ባለሀብቶችን በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል የኢንቨስትመንት ቢሮ ፕሮጀክቱ በትክክል በቦታው መኖሩ ሳይረጋገጥ /ግንባታው ሳይኖር/ እየተፈቀደ የሚገኝና ከ2005-2007 ዓ.ም የቀረጥ ነጻ ጥያቄ ላቀረቡበት ሥራ ሳይሆን ብረት ለመሸጥ ሲሉ ብቻ በሀሰተኛ ሰነዶች/አድራሻ/ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻው መብት ተጠቃሚ በመሆን ያስገቡትን የፌሮ ብረት ለጠየቁት አላማ ሳይሆን ያለአግባብ ለሽያጭ ያቀረቡ ባለሀብቶች መኖራቸው የኦዲት ቡድኑ ከጉምሩክ አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ከኢንተለጀንስ ክፍል በተገኘና በተከለሰ መረጃ ለማወቅ ችሏል፡፡ መረጃውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- አቶ ኢብራሂም አደም የተባሉ ባለሀብት የብረት ማቅለጫ ፋብሪካ ለመገንባት በሚል በአማራና ኦሮሚያ ክልል ፍቃድ የወሰዱና የጉምሩክ የቀረጥ ነጻ ድጋፍ የጠየቁበት የኢንቨስትመንት ግንባታውም በቦታው የሌለ ሲሆን 14,491.54 ሜትሪክ ቶን ፌሮ ብረት ብር 98,019,097.36 (ዘጠና ስምንት ሚሊዮን አሥራ ዘጠኝ ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሰላሳ ስድስት ሳንቲም)ከቀረጥ

ነፃ በማስገባትና ለገበያ ሽያጭ ማዋላቸው በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

- አቶ መሀመድ ከድር አብዱ በሚል መጠሪያ ሀሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት በኦሮሚያ ክልል ሆቴል ለማቋቋም በሚል 466,689 ሜትሪክ ቶን ፌሮ ብረት ከቀረጥ ነፃ ብር ብር 2,710,324.61(ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ አሥራ ሺህ ሦስት መቶ ሃያ አራት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም) ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባትና አላግባባ ለገበያ ሽያጭ ማዋላቸው በኦዲቱ ወቅት በተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- አቶ አሰፋ ሙሄ አሊ በሚል መጠሪያ ሀሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት በኦሮሚያ ክልል ለመቋቋም ላቀዱት ሆቴል ግንባታ በሚል 520 ሜትሪክ ቶን ፌሮ ብረት ብር 3,921,776.51 (ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከሃምሳ አንድ ሳንቲም) ሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ በማስገባትና ለሽያጭ ማዋላቸው በኦዲቱ ወቅት ቢሮ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- አቶ አህመድ እንድሪስ አሊ በሚል መጠሪያ ሀሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት በኦሮሚያ ክልል ለማቋቋም ላቀዱት ሆቴል ግንባታ የሚውል በሚል 580 ሜትሪክ ቶን ፌሮ ብረት ብር 3,413,721.79 (ሦስት አራት መቶ አሥራ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አንድ ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባትና አላግባብ ለሽያጭ ያዋሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡
- አቶ ካሳሁን ጌታቸው አልታየ በኦሮሚያ ክልል ለማቋቋም ላቀዱት ሆቴል እና ት/ቤት ግንባታ የሚውል በሚል ኢንቨስትመንቱ በቦታው ያልተቋቋመ ቢሆንም 1419 ሜትሪክ ቶን ፌሮ ብረት ብር 9,642,803.35 ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡ ቢሆንም ያስገቡትን ብረት አላግባብ በሽያጭ ያዋሉ በመሆኑ በጠቅላላ ብር 117,707,723.62 (አንድ መቶ አስራ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ሦስት ብር ከስልሳ ሁለት ሳንቲም) ያለአግባብ ከቀረጥ ነጻ መግባታቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. ስለጉዳዩ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በመንግሥት የተሰጡ መብቶች ማስፈፀሚያ ኃላፊ ተጠይቀው ሲገልጹ የግንባታ ዕቃዎች ላይ ባለሀብቱ

በሚያቀርበው ቢል ኦፊ ኳንቲቲ መሠረትና ኢንቨስትመንቱ ቦታው ላይ መኖሩ ሳይረጋገጥ በወረቀት ላይ ብቻ እየጸደቀ መሆኑ የኢንቨስትመንት ፍቃዱን የሚሰጡት የኢንቨስትመንት ቢሮዎች እንደመሆናቸው ማረጋገጥ ሥራ የነሱ መሆኑን በተለይ ብረት ላይ ችግር መኖሩና ስታንዳርድ ሊወጣለት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ የህግ ማስከበር ክፍል ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቀረጥ ነፃ መብት አለአግባብ መገልገል ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ ክትትል መደረጉ የሚከብድ መሆኑን አብዛኛውን ጊዜ ሽያጭ የሚፈጸመው አየር በአየርና ያለደረሰኝ በመሆኑ ያለአግባብ ስለመገልገሉ በወቅቱ ለማረጋገጥ ስለሚያስቸግር የቀረጥ ነፃ ከመፈቀዱ በፊት የኢንቨስትመንት ቢሮዎቹ ዕቃውን ሲፈቅዱ ጥንቃቄ ማድረግና ኘሮጀክቱ ባለበት አካባቢ ያሉት የአስተዳደር አካላት ክትትል እንዲደርጉ መደረግ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

48. በተመሳሳይ ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈጸሚያ ኃላፊ የግንባታ ዕቃን አስመልክቶ የመንግሥት አካል ካላጸደቀ እንደማይፈቅዱ ነገር ግን አዲስ አበባ መስተዳደር ስለማያጸድቅ አሰራራቸው ላይ ክፍተት መፍጠሩን እንዲሁም ኢንቨስትመንቱ ቦታው ድረስ በመሄድ የሚያረጋግጡት የተሽከርካሪ የቀረጥ ነፃ ይገባኛል ጥያቄ ሲመጣ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

49. በመሆኑም የኢንቨስትመንት ቢሮዎች በትክክል ኢንቨስትመንቱ በቦታው መኖሩን ሳያረጋግጡ መፍቀዳቸውና የኢንቨስትመንት ማበረታቻውን አላማ የሚጻረርና አገሪቱ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ያለአግባብ እንድታጣ ያደርጋታል፡፡

50. በኦዲቱ ከተዩት በሁሉም የክልል መስተዳደርና የከተማ ኢንቨስትመንት ቢሮዎች የካፒታል ዕቃዎች በመጠን ወይም በዓይነት የተገደበ ህግ ባለመኖሩ ባለሀብቱ የጠየቁትን የጉምሩክ የቀረጥ ነጻ ድጋፍ በሙሉ የሚያሳልፉ መሆኑንና በዚህ ሁለት አመት ውስጥ በ2006 ዓ.ም.ና በ2007 ዓ.ም. ለቢራ ፋብሪካዎች በጠቅላላ ከብር 700,000,000/ሰባት መቶ ሚሊዮን/ እስከ ብር 1,000,000,000 /አንድ ቢሊዮን/በላይ ለአንድ ድርጅት እየተፈቀደ መሆኑ ታውቋል፡፡ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስመንት ፍቃድ ካወጡት ድርጅቶች ውስጥ ለአብነት ያህል ዳሽን

ቢራ ፋብሪካ ብር 1,599,068,553.19/አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ሦስት ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም /፣ ሂኒከን ቢራ ፋብሪካ ብር 1,985,865,246.00/አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ስድስት ብር/፣ ሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ ብር 834,173,389.70/ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሳንቲም/ና ራያ ቢራ ፋብሪካ ብር 764,405,418.30/ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሚሊዮን አራት መቶ አምስት ሺህ አራት መቶ አሥራ ስምንት ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ በሁለት አመት ውስጥ እንዲያገኙ በኮሚሽኑ መፈቀዱን በኦዲት ወቅት ጉዳዮን አስመልክቶ ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በመንግሥት የተሰጡ መብቶች ማስፈፀሚያ ኃላፊ ተጠይቀው ሲገልጹ የካፒታል ዕቃንም አስመልክቶ አግባብነቱን ማረጋገጥ ያለባቸው ድጋፍ የሚጽፉት ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ቢሆኑም ለማስፋፊያ ተብሎ ዝም ብሎ እየተፈቀደም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

52. የኦዲት ቡድኑ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከመፍቀድ ውጭ አገሪቱ ማበረቻውን በመስጠቷ የምታጣው ጥቅምና ባለሀብቱ የሚያስገኘው ጥቅም በንጽጽር የማይገመገም መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. ኮሚሽኑ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በተሰጠው መልስ የካፒታል ዕቃዎች ያለገደብ መፈቀዳቸውን አስመልክቶ በደንብ ቁጥር 270/2005 ላይ በካፒታል መጠንና በቀጠሩት ቋሚ የሰው ኃይል እንደተገደበ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ላይ የሥራ መስኮች ተዘርዝረው መቀመጣቸውን፣ ማበረታቻ የሚሰጡ ተወዳዳሪ የሆኑ አገሮች በርካቶች በመሆናቸው አገራችን ኢንቨስትመንት ማበረታት የምትችለው ከሌላው ሀገር በተሻለ ሁኔታ ማበረታቻዎችን በመስጠት ጭምር እንደሆነ እንዲሁም አገሪቷ ማበረታቻውን በመስጠቷ ያስገኘው ጥቅም በኮሚሽኑ የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በኩል በማይክሮ /ኢንተርፕራይዝ/ ደረጃ የሚገመገም መሆኑንና

በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ፋይዳ በተመለከተ በኮሚሽኑ ደረጃ ስትራክቸርድ የሆነ ጥናት ለማስጠናት ቅድመ ዝግጅት መጀመሩ ተገልጿል፡፡

54. ይሁን እንጂ ከላይ በተራ ቁጥር 27 እንደተገለጸው የተገደበው በመጠን አለመሆኑና እንዲሁም በአንቀጽ 13 ላይም የተገለጸው የዕቃው ዝርዝር እንደተሸከርካሪ መመሪያ ተመጥኖ ሳይሆን የሥራ መስኩ እና የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ አስመልክቶ መሆኑ፤ እንዲሁም አገሪቷ ማበረታቻውን በመስጠቷ የተገኘውን ፋይዳ መገምገሙን በተመለከተ በኮሚሽኑ የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በመሰጠቱ አገሪቷ እያገኘች ያለውን ጥቅም አለመገምገሙ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ባለሀብቱ መንግሥት በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ተጠቃሚ
<u>ለመሆን አስቀድሞ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርብ መደረጉን በተመለከተ</u>፤

55. ከቀረጥ ነፃም ሆነ ከገቢ ግብር ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆን ማንኛውም ባለሀብት አስፈላጊውን መረጃ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት ቢሮ ወይም የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃ አስቀድመው ሳያቀርቡ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስተናግዳቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት በኮሚሽኑ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተለከሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

57. በኢንቨስትመንት የሚሳተፉ ባለሀብቶች መለዋዋጫዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለሚያቀርቡት ጥያቄ ለመፍቀድ በኮሚሽኑ ከሚታዩ ጉዳዮች አንዱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተጠየቁት መለዋዎጫዎች ባለሀብቱ ከውጭ ካስገባቸው ጠቅላላ የካፒታ ዕቃዎች ዋጋ ከ 15% ያልበለጡ መሆኑን ማየት ቢሆንም ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ በኢንቮይስ ቁጥር 7411 PN96906738c፣ 1010024670፣ 13BW1032፣ 006፣ 10-DMC 160፣ 741 PN196906736፣ 9960220 ያስገባቸው የመለዋወጫ ዕቃዎች የየትኛው የካፒታል ዕቃ መሆኑና ከ15% ያልበለጡ ስለመሆናቸው ማቀናነሻውን ሳይያያዝ /ሳይታይ/እንዲገባ መፈቀዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. እንዲሁም ሚድሮክ ኢትዮጵያ በኢንቫይስ ቁጥር 2013-JAN-004፣ 2013-JAN-005፣ 2013-JAN-006፣ 2013-JAN-007፣ 2013-JAN-008፣ 2013-JAN-010፣ 2013-JAN-012፣ 2013-JAN-014፣ 2013-JAN-015፣ 2013-JAN-016፣ 2013-JAN-017፣ 2013-JAN-018፣ 2013-JAN-019፣ 2013-JAN-020፣ 2013-JAN-021፣ VPF46115575፣ S302323፣ S302337፣ IPD-283-CR-13 ያስገባቸው ዕቃዎች ከኮሜርሽያል ኢንቮይስ ውጭ መመሪያው በሚያዘው መሠረት ሌሎች መቅረብ ያለባቸውን /የማስጫኛ ሰነድ ፎቶ ኮፒ (Bill of Lading/Air way bill/truck way bill) ፎቶ ኮፒ..../መረጃዎች ያልቀረቡ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

59. ኤስ. ደብልዩ. ኤስ የተባለ ድርጅት በሰኔ 2007 .ዓ.ም 21 ጀነሬተር ምንም መረጃ ሳያቀርብ ለሦስት ወር ጊዜ ኢንሹራንስ ቦንድ እንዲያሲዝና እንዲያስገባ በኮሚሽኑ የተፈቀደለት ሲሆን በተጨማሪም ለሦስት ወራት በመስከረም 2008 ዓ.ም. እንዲራዘምለት የጠየቀና ኮሚሽኑም የፈቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. በተመሳሳይ መልኩ ኢቱር ቴክስታየል በ5/4/2005 በኢንቫይስ ቁጥር 013/12፣ 025፣ 300892 በ29/11/2005፣ በኢንቮይስ ቁጥር 343837፣ የመለዋወጫ ዕቃዎችን ከኮሜርሻል ኢንቮይስ በስተቀር ሌላ መረጃዎችን ሳያቀርብ የጉምሩክ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆን የተፈቀደለት ሲሆን የመለዋወጫ ዕቃዎቹም ዋጋ ከጠቅላላ የካፒታል ዕቃው ዋጋ ከ15 በመቶ ያልበለጠ መሆኑን የሚያሳይ/ ማቀናነሻም እንዳልቀረበ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በኢንቮይስ ቁጥር 23449፣ 23475፣ 343835፣ 047፣ 046፣ ያስገባቸው የግንባታ ዕቃዎች ቢል ኦፍ ኳንቲቲ ሳያቀርብ በኮሚሽኑ የጉምሩክ ከቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ እንዲሆን የተፈቀደለት መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

61. ሞሐ ለስላሳ ፋብሪካ ማቅረብ የነበረበትን ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማስፈጸሚያ መመሪያ 8.2.3/ሀ/3 ላይ ፕሮጀክቶች የመለዋወጫ ዕቃ ለማስገባት መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ ድርጅቱ ሳያቀርብ መፈቀዱን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. ከላይ የተገለጸውን ጉዳይ አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በትክክል ባለሀብቶች የሚያቀርቡት የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ተጠቃሚነትን አስመልከቶ ሥራውን እየሰራው ያለው ጉምሩክ በመሆኑ እያንዳንዱ መረጃ ማየት ያለበት ጉምሩክ መሆኑንና ኮሚሽኑ የሚያስቀረው ኮፒውን በመሆኑ ምናልባት ገጾቹ ተገንጥለው ሊሆን ስለሚችል የኦዲት ቡድኑ ይህንን እንዲያረጋግጥ ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ተላከ የተባለው የአባሪ ብዛትና የኦዲት ቡድኑ ከመረጃው ያገኘው ገጽ ብዛት ተመሳሳይ በመሆኑና የቀረጥ ነፃ ማስፈጸሚያ መመሪያ ላይ ኮሚሽኑ መረጃዎቹ አይቶ መፍቀድ እንዳለበት የሚገልጽ በመሆኑ በኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ኮሚሽኑ በመመሪያው መሠረት አለመስራቱ መስፈርቱን የማያሟሉ ፕሮጀክቶች ያለአግባብ የጉምሩክ ከቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የኢኮኖሚ ጥቅም አሳጥቷል፡፡ አሠራሩም ለህግ ወጥነት በር የሚከፍት በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ኮሚሽኑ በደንብ ቁጥር 270/2005 መሠረት የካፒታልና

<u>የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መፍቀዱን በተመለከተ፤</u>

63. በደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ አስራ አንድ ቁጥር አንድ ላይ ማንኛውም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት እንደሚችል ይገልጻል፡፡

64. ይሁን እንጂ ማንኛውም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማስገባት እንደሚችል በኦዲቱ ወቅት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ቁጥር አንድ ላይ በተገለጸው መሰረት የኮሚሽኑ አፈጻጸምን አስመልክቶ በተደረገው ማጣራት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ቦርድ አፈጻጸም በደንቡ ከተገለጸው ውጭ የጉምሩክ የቀረጥ ነጻ ፍቃድ እየፈቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ናይል ዲቨሎኘመንት የተባለ ድርጅት በ19/2/96 የኢንቨስትመንት ፍቃድ በ1997 ደግሞ የንግድ ፍቃድ አውጥቶ በግብርና ላይ የተሰማራ ሲሆን ከ1997 ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ለኘሮጀክቱ የሚሆኑ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ እያስገባ ያለና በሌሎች ማለትም በአይን መነፅር፣ በከብትና በንብ እርባታ 28/2/2001፣ 16/4/2004ና የኢንቨስትመንት ፍቃድያወጣ ቢሆንም በግብርናው ግን ለማስፋፊያ የሚሆን የኢንቨስትመንተ ፍቃድ ያላወጣ ሲሆን ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የእርሻ መሳሪያዎች፣ አክሰሰሪዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች ከነመለዋወጫቸው በ2005ና በ2006 ዓ.ም. የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ እንዲሁም በግብርና ላይ ለተሰማራ ባለሀብት ግሬደርና ዳምፐር በደንቡ መሠረት እንዲያስገባ የማይፈቀድ ቢሆንም የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆን ከዚህ በተጨማሪም ይህ ድርጅት የቪድዮ፣ የፎቶና የቴሌቪዥን ካሜራዎች እንዲሁም የፀሐይ ውሃ ማሞቂያ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ቦርዱ የፈቀደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም ደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ በ1998 ዓ.ም. የተመሰረተና በ2005 ዓ.ም ንግድ ፍቃድ ያወጣ ሲሆን ለማስፋፊያ የሚያስፈልገውን ፈቃድ ያላወጣ ቢሆንም ከደንቡ ውጭ የአሳንሰር ዕቃዎች /Material of elevator/ በቦርዱ የተፈቀደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከኮሚሽኑ በተገኙ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም ይኸው ድርጅት በታህሳስ 2006 ዓ.ም. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በ2007 ዓ.ም. ለመለዋወጫ ዕቃዎች ብቻ መፍቀዱን ከኮሚሽኑ መረጃ ማወቅ የተቻለ እንዲሁም በ2006 ዓ.ም. ቦርዱ ስለመፍቀዱ በቦርዱ ቃለ ጉባኤ ላይ መረጃ ያልተገኘ ቢሆንም ከጉምሩክ የመረጃ ቋት ግን መስከረም 2006 ዓ.ም. DUMPERS FOR OFF-HIGHWAY USE ወይም VOLVO FH 64T TRACK TRACTOR WITH GORCIA TIPP. (AAK/IP) 150 መጠን /ብር 67,940,816.4 የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ያስገባ መሆኑን ከጉምሩክ የመረጃ ቋት ለመረዳት ተችሏል፡፡

65. በተጨማሪም በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 ላይ የካፒታል ዕቃ ማለት ለኘሮጀክቱ ምርት ለማምረት የሚያስችሉ ወይም አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የማምረቻ መሣሪያዎች መሆናቸው የተገለጸ ቢሆንም ከደንቡ ውጭ በኢንቨስትመንት የተሳተፉ ባለሀብቶች በቦርዱ ፈቃድ የጉምሩክ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንደተደረጉ

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ዝርዝር ጉዳዮም እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ጆርጅ ሹ የተባለ የጫማ ፋብሪካ ድርጅት በ2006 ዓ.ም. የመስመር ስልኮች፣ የኪችን ቁሳቁሶች የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ ኦቨን፣ ፍሪጅ....፣ የተለያዩ እስክሪብቶዎች፣ የፎቶግራፍ ፊልሞች፣ የፋይል አቃፊዎች/folders/፣ ባይንደሮች፣ ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች፣ ዲጂታል ካሜራዎችና ቪዲዮ ካሜራዎች፣ የእንጨት ዕቃዎች /wood furnitures/፣ ፕሮጀክተሮች፣ ስቱዲዮ ሳውንድ ሲስተሞች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ time attendance machine፣ የቢሮ፣ የወርክሾፕ፣ የኮንፍረንስ ወንበሮች፣ የቢሮ ጠረጴዛዎች፣ ፋይል ካቢኔት፣ ኤር ኮንዲሽነር፣ ...../ ከብር 1,487,374.02 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሰባ አራት ብር ከሁለት ሳንቲም) በላይ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገባ መፈቀዱ፣ በተጨማሪም ይህ ድርጅት ለጫማ ፋብሪካ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ዞን ተከራይቶ ላቋቋመው ድርጅት ቤቱ የሚመለከተው አካል ቢያድሰውም አሁንም እያፈሰሰ ነው በሚል በደንብ 270/2005 አዲስ ወይም ለሚያስፋፋው ድርጅት የግንባታ ዕቃ እንደሚፈቀድለት ቢገልጽም ወደ ሥራ የገባው ተከራይቶ እንጂ የራሱ ባልሆነ ህንፃ መሆኑና አዲስ በወጣው በደንብ ቁጥር 213/2006 የግንባታ ዕቃ ከቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆን የማይፈቅድ ቢሆንም ብር 241,772.27 (ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺ ሰባት መቶ ሰባ ሁለት ብር ሃያ ሰባት ሳንቲም) ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆን በቦርዱ እንደተፈቀደለት በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።
- እንዲሁም ዳሽን ቢራ ፋብሪካ በ2007 ዓ.ም. 14 የቴሌቪዥን፣ ዲጅታልና የቪድዮ ካሜራዎች ብር 445,925.55፣ ኬይ ኢንዱስትሪ ኢንጅነሪንግ አማካሪ የቻይና ድርጅት ሲሆን ድርጅቱ ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነፃ 20,000 (ሀያ ሺ) time recorder card accessories ብር 28,453,.88 (ሃያ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሦስት ብር ከሰማንያ ስምንት ሳንቲም ብር) እና ብር 15,200 (አስራ አምስት ሺ ሁለት መቶ) የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ በመሆን ዕቃዎቹን እንዲያስገባ በቦርዱ እንደተፈቀደለት በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል።
- ኤም.ኤን.ኤስ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር የተባለ የውጭ ባለሀብት በጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሥራ መስክ የተሰማራ ሲሆን በ2006 ዓ.ም. ከቀረጥና ታክስ ነፃ 490X190፣ 2 200X15 አልጋ፣ 4 ሶፋ ፣ ኮምፒውተሮች ከነአክሰሰሪዎቹ እና 2

metal capinet ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ በቦርዱ ተፈቅዶለት እንዳስገባ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- እንዲሁም ዶንግ ፋንግ የተባለ ድርጅት ጨርቃ ጨርቅ የሚሸምን የሚያጠናቅቅና የሚያትም ድርጅት ሲሆን ድርጅቶች ጥሬ ዕቃዎችን እንዲያስገቡ የተደነገገ ህግ የሌለ ቢሆንም ቦርዱ በኮሚሽኑ ስም የካቲት 2005 ዓ.ም. ጥሬ ዕቃዎችን እንዲያስገባ የመግባቢያ ስምምነት የተፈራረመና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ለምርት የሚሆን የጨርቃ ጨርቅ ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ በገንዘብ ሚኒስቴር እየተፈቀደ እስከ የካቲት 2007 ዓ.ም. ድረስ ሲያስገባ መቆየቱ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ኬይ ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪን ኮንሰልታንሲ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት saving light and fluorescent lamp ሊከፈል የሚገባ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ 682,041.13(ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺህ አርባ አንድ ብር ከአሥራ ሦስት ሳንቲም) ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ እንደካፒታል ዕቃ በመቁጠር ያለአግባብ ቦርዱ እየፈቀደ መሆኑን ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትና ከጉምሩክ የመረጃ ቋት በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ ዳይሬክተር በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እንደክፍል የክፍሉ ኤክስፐርቶች ጋር በመሆን በተቻለ መጠን መመሪያ ተከትለው እየሰሩ መሆኑን ነገር ግን ሥራው ለሁለት እየተሰራ ማለትም ቦርዱም እየፈቀደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

67. እንዲሁም ኮሚሽኑ የፈቀላዳቸውና ከጉምሩክ የመረጃ ቋት የተገኙና በትክክል የገቡ ዕቃዎች ልዩነት ያላቸው መሆኑና በ2007 ዓ.ም. ኤስ.ደብልዩ.ኤስ የተባለ ድርጅት ለኮንስትራክሽን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ በ2007 ዓ.ም. ለካፒታል ዕቃዎችና ለመለዋወጫዎች ብር 19,989,340.6938 ተጠቃሚ እንዲሆን መፈቀዱን የኮሚሽኑ መረጃ የሚያሳይ ቢሆንም ነገር ግን ከጉምሩክ መረጃ ቋት እንደተገኘው ወደ ብር 90,005,644 ከቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ዕቃዎች ማለትም በልዩነት ብር 70,016,303.31 መግባታቸው የሚያሳይ መሆኑ በኮሚሽኑ መረጃና ከጉምሩክ የመረጃ ቋት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤

68. ስለጉዳዩ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ ዳይሬክተር በጉምሩክ መረጃ ቋትና በኮሚሽኑ ከቀረጥ ነፃ የገባ ዕቃዎች የመረጃ ልዩነት በተመለከተ ቦርዱ የሚፈቀደውን ዕቃዎች በነሱ መረጃ ላይ የማያስገቡ መሆኑንና አንዳንድ ባለሀብቶች ኢንቮይሱን አሳንሰው ወይም አስበልጠው ሊያስገቡ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

69. በመሆኑም የኢንቨስትመንት ቦርዱ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 29 ቁጥር 6 ላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥራ ላይ ካለው ደንብ በተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል በሚለው መሰረት ቦርዱ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ ማቅረብ ቢኖርበትም በ2005 እና በ2006 ዓ.ም. በራሱ እየወሰነ የሚገኝና ከደንቡ ውጭ ዕቃዎች ያለአግባብ እየፈቀደ የሚገኝ በመሆኑ አገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ በማድረግ ህግን ያልተከተለ አሰራር እንዲስፋፋ በር ሊከፍት ይችላል፡፡

70. ኮሚሽኑ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በተራ ቁጥር 69 ላይ የቦርዱን ስልጣን በተመለከተ በሰጠው መልስ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 270/2004 ማሻሻያ እንደተደረገበት ተገልጿል፡፡

71. በመሆኑም የቦርዱን ስልጣን በተመለከተ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 270/2004 ማሻሻያ የተደረገው በሐምሌ 15 ቀን 2006 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 849/2006 ሲሆን ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው በ2007 በጀት ዓመት ሲሆን ቦርዱ ከላይ እንደተመለከትነው አብዛኛውን የፈቀደው በ2005 እና 2006 ዓ.ም. በመሆኑ በድጋሚ ነሐሴ 8 2006 ዓ.ም ማለትም ከ15 ቀን በኋላ ደንብ ቁጥር 313/2006 የወጣና ማሻሻያ በድጋሚ የተደረገ ሲሆን በአዋጁ ቁጥር 270/2004 አንቀጽ 29 እና አግባብ ባላቸው ሌሎች አዋጆች ድንጋጌዎችን የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ይውላል የሚል በመሆኑና ቦርዱ ጥሬ ዕቃውን አስመልክቶ ከመመሪያው ውጭ መፍቀዱ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚያስገባቸው የሚፈቀዱ የመለዋወጫ
<u>ዕቃዎች ደንብ 270/2005 መሠረት ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ</u>፤

72. የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ቁጥር 4 ላይ ኮሚሽኑ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል እቃዎች ጠቅላላ ዋጋ 15 በመቶ የማይበልጡ መለዋወጫዎችን ፕሮጀክቱ ማምረት

ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት አመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ሊፈቅድ ይገባል ቢልም ኮሚሽኑ ከመመሪያ ውጭ ፕሮጀክቶች ማምረት ሳይጀምሩ እና ምን ያህል ማስገባት እንዳለባቸው /የካፒታል ዕቃው 15 በመቶ መሆኑን ሳይረጋግጥ እንደፈቀደ ታውቋል፡፡

73. ኢቱር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የንግድ ፍቃድ ያወጣና ወደ ምርት የገባው በ26/05/2006 ሲሆን ነገር ግን የመለዋወጫ ዕቃዎች ማምረት ሳይጀምር በ2/4/2005 በኢንቫይስ ቁጥር 013/10፣ 011ና 013/12፣ 025፣ 026 በ29/11/2005 በኢንቮይስ ቁጥር 343837፣ በ9/1/2006 በኢንቮይስ ቁጥር 300892፣ 11/02/06 በኢንቮይስ ቁጥር 043ና 044ና 24608 ያመጣቸውን የመለዋወጫ ዕቃዎች ከደንቡ ውጭ ያለአግባብ እንደተፈቀደለት በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

74. ዳሸን ፋብሪካ ለሦስተኛው ማስፋፊያ የሚሆን የመለዋወጫ ዕቃ ድርጅቱ ሥራ ሳይጀምር ድርጅቱ በይፋ ሥራ የጀመረው በ2008 ዓ.ም. ሲሆን /ጥር፣ መጋቢትና ሚያዝያ 2006 ዓ.ም. ምን ያህል ማስገባት እንዳለበት ማቃነሻም ሳያቀርብ መፈቀዱ፣ ዶንግፋንግ የተባለ ድርጅት ኢንቨስትመንት ፍቃድ ሰኔ 2005 ዓ.ም. ንግድ ፍቃድ በሰኔ 2006 ዓ.ም. ያገኘ ሲሆን በጥር 2006 ዓ.ም. ወደፊት የሚታሰብ በሚል ሥራ ሳይጀምር የመለዋወጫ ዕቃዎች እንዲያስገባ መፈቀዱ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

75. በተመሳሳይ መልኩ ደርባ ሚድሮ ሲሚንቶ ፋብሪካ በ2007 ዓ.ም. 98,133,596.00 ለመለዋወጫዎች የቀረጥና ታክስ ነፃ ማበረታቻ በኮሚሽኑ የተፈቀደለት ሲሆን በኢንቫይስ ቁጥር 7411፣ PN96906738c፣ 1010024670፣ 13BW1032፣ 006፣ 10-DMC 160፣ 741 PN196906736፣ 9960220 ያስመጣቸው መለዋወጫ ዕቃች 15 በመቶው ሳይሰላና ምን ያህል መፈቀድ እንዳለበት ትክክለኛ መረጃ መሠረት ሳያደርግ ወደፊት ታሳቢ የሚሆን በሚል እንዲገባ መፈቀዱ፣

76. እንዲሁም ሚድሮክ ኢትዮጵያ /ለሆቴል/ህጉ ከሚፈቅደው ወጭ በ9/7/05 ጀነሬተር በራሱ እንደካፒታል ዕቃ መቆጠር የሌለበት ቢሆንም እንደካፒታል ዕቃ እየተቆጠረ ያለ ሲሆን እንደኮሚሽኑ አካሄድ እንደ ካፒታል ዕቃ ቢቆጠር እንኳን ፕሮጀክቱ ገና ወደ ሥራ ሳይገባና 15 በመቶው ሳይሰላና ምን ያህል መግባት እንዳለበት ሳይታወቅ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

77. በሌላ መልኩ ጆርጅ ሹ የጫማ ፋብሪካ በየካቲት 19 ቀን 2007 ዓ.ም. መለዋወጫ ዕቃ 15 በመቶው ሳይሰላና መጠኑ ሳይታወቅ እንዲገባ ሲፈቀድለት፣ ናይል ዲቨሎኘመንት የተባለ ድርጅት በተለያየ የሥራ መስክ የተሰማራ ሲሆን በ19/2/96 የኢንቨስትመንት ፍቃድና በ1997 የንግድ ፍቃድም አውጥቶ እየሰራ የነበረና በተጨማሪም በዘርፉ የማስፋፋያ ፍቃድ ያላወጣ ሲሆን በደንቡ መሠረት ማምረት ከጀመረበት እስከ አምስት አመት ብቻ ባለሀብቶች እንዲያገኙ የተደነገገ ቢሆንም ድርጅቱ ግን ከ15 አመት በላይ ዕድሜ ያለው ሲሆን የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያስገባ በጳጉሜ 2005 ዓ.ም. በቦርዱ እንደተፈቀደለት በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ሞሐ ለስላሳ ፋብሪካ ከ26/7/2007 ጀምሮ መቀሌ በሚገኘው የለስላሳ ፋብሪካው ሥራ የጀመረ ቢሆንም ኮሚሽኑ ነሐሴ 16/2006 ዓ.ምና መስከረም 7/2007 ዓ.ም. ብር 193,009.09 (መቶ ዘጠና ሦስት ሺህ ዘጠኝ ሺህ ብር ከዘጠኝ ሳንቲም) ከመመሪያው ውጭ መፍቀዱ ከኮሚሽኑ በኦዲቱ ወቅት በተገኙና በተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በኮሚሽኑ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከ15 በመቶ እስካልበለጠ ለምን አንፈቅድም በሚል ሲፈቀዱ የነበረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ቦርዱን ሲጠይቁት መፈቀድ የለበትም በማለቱ መፍቀድ ማቆማቸውን አስረድተዋል፡፡ ኃላፊው በተጨማሪም እንደአሰራር ጥሩ የማይሆነው ከ15 በመቶ ከበለጠ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

79. ይሁን እንጂ አንድ ድርጅት እንደአሰራርም መለዋወጫ ዕቃዎች ሊፈቀድ የሚገባው ድርጅቶች ወደ ሥራ ከገቡና የካታል ዕቃዎች ብልሽት ሲያጋጥማቸው መሆነ ያለበት በመሆኑ የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊ የሰጡትን መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም አሠራሩ በደንብ ቁጥር 270/2005 ከተገለጸው በተጻረረ ወይም ከደንብ ውጭ መፈጸሙ አሠራሩ ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አሳጥቷል፡፡

80. በኮሚሽኑ የኦዲት ሪፖርቱ ላይ በተሰጠው መልስ ከደንቡ ውጭ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀዱ የመለዋወጫ ዕቃዎችን አስመልክቶ ኘሮጀክቶቹ የካፒታል ዕቃዎችን ማለትም የማምረቻ መሳሪያዎችን አስመርተው የሚያስጭኑ በመሆኑ ቦርዱ በልዩ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ማድረጉና ይህ የማይፈቀድ ከሆነና ከካፒታል ዕቃዎቹ ጋር መለዋወጫዎቹን ማምጣት ካልቻሉ የማምረቻ መሳሪያ ያመረተው ድርጅት ሊዘጋ ወይም የሚያመርተውን ምርት ሊቀይር ስለሚችል ድርጅቶች ካላቸው ስጋት መሆኑን

እንዲሁም ጆርጅ ሹ የተባለው የጫማ ፋብሪካ አንድ ፋብሪካ ሳይሆን ከ24 በላይ ፋብሪካዎችን በመገንባት ላይ የሚገኝና ራሱን የቻለ ሌላ ስምምነት ያለው የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ በመሆኑ በዚሁ አግባብ የተፈጸመ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

81. ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ቁጥር 4 ላይ ኮሚሽኑ ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት አመት ድረስ የመለዋወጫ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የሚፈቅድ በመሆኑና ፕሮጀክቶቹ በትክክል አስመርተው ይሁን ገበያ ላይ ያለውን ገዝተው ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ ባለመኖሩና ገና ለገና አምራች ድርጅቱ ሊዘጋ ይችላል በሚል የተሰጠው ምክንያት ከደንብ ውጭ ለመፈጸም አጥጋቢ የሆነ ምክንያት አለመሆኑ፣ እንዲሁም ጆርጅ ሹ የተባለው ድርጅት በቀን የካቲት 19ና 20 ቀን 2007 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር ቀ/ነ/17/11123/2359 በተጻፈ ደብዳቤ የጠየቀው ለቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ዞን ላቋቋመው የጫማ ፋብሪካ ብቻ መሆኑን በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ኮሚሽኑም ሆነ ቦርዱ ከደንቡ ውጭ መፍቀዳቸው አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጪ እንዲያስገባቸው የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች መመሪያውን መሰረት ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ</u>፤

82. ኮሚሽኑ ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጪ እንዲገቡ የሚፈቅደው የተሽከርካሪዎች ዓይነት እና ብዛት በስራ መስክ እና በሚቋቋምበት የልማት አካባቢ ቦርዱ መጋቢት 4 ቀን 2005 ባወጣው መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን መጋቢት 2005 ዓ.ም. ከወጣው መመሪያ ውጭ የኢንቨስትመንት የሥራ አመራር ቦርድ እየፈቀደ ይገኛል፡፡

84. ሱር ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ አንድ በሕንፃና በመንገድ ሥራ የተሰማራ ድርጅት ሲሆን ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ አንቀጽ 6 ሠንጠረዥ 3 ቁጥር 3/3.3 ላይ በመንገድ ሥራ ተቋራጭ ላይ የተሰማራ ባለሀብት የውሃ መርጫ የተገጠመለት መኪና 2 የሚፈቀድ ቢሆንም 30 የውሃ መርጫ የተገጠመለት መኪና ሊከፍል የሚገባውን ብር 8,682,276.83 (ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ሰማንያ

ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሰማንያ ሦስት ሳንቲም)ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ ያለ አግባብ ቦርዱ የፈቀደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. ኤስ.ደብልዩ.ኤስ የተባለ የቻይና ድርጅት በኮንስትራክሽን ዘርፍ በደረጃ አንድ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት ስራ የተሰማራ ሲሆን የወጣውን የተሽከርካሪ መመሪያ በጣሰ መልኩ ሁለት ላንድ ክሩዘር፣ መክፈል የነበረበት የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ 3,640,394.94(ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም/ እንዲሁም ሁለት ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መክፈል የነበረበት የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ 3,468,659.66 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ ስድስት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም) በተጨማሪም ይህ ድርጅት የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፍቃድ በ14/10/2007 ያገኘ ሲሆን ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ሰንጠረዥ 3 ቁጥር 1.2 ላይ ለጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ አንድ የተፈቀደው የውሃ መያዣ መኪና 1 ብቻ የተፈቀደና ለማስፋፊያው በተጨማሪም 1 በጠቅላላ 2 መፈቀድ ቢኖርበትም ድርጅቱ ግን 4 የሚሆኑ በጠቅላላ ብር 608,201.665 /ስድስት መቶ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አንድ ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ሳይከፍል ያስገባ መሆኑና በድምሩ 7,717,256.27 ብር (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ አስራ ሰባት ሁለት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺህ ከሃያ ሰባት ሳንቲም) በቦርዱ ፍቃድ ያለአግባብ ከቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ መሆኑ ታውቋል፡፡

86. ጆርጅ ሹ የተባለ የቻይና ድርጅት በጫማ ፋብሪካ፣ በኢንዱስትሪ ዞን ግንባታና በጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ የስራ መስክ የተሰማራ ሲሆን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል በቁጥር 13 ብስክሌቶች ሊከፈል የሚገባ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ 4,924.21 ብር/አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ አራት ከሃያ አንድ ሳንቲም/፣ 1 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር 4,583,084.74 ብር /አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ከሰማንያ ሦስት ሰማንያ አራት ከሰባ አራት ሳንቲም/፣ 5 isuzu truck ከዚህ ብረ 1,014,135.96 ብር/አንድ ሚሊዮን አሥራ አራት ሺና መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም/፣ 1 fuel truck ብር 344,940.05 /ሦስት መቶ አርባ አራት ሺህ ዘጠኝ አርባ ከአምስት ሳንቲም/፣ 4 toyota wish ብር 4,844,465.35 /አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺህ ከአራት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም/በጠቅላላው ብር

10,831,550.31 /አሥር ሚሊዮን ስምን መቶ ሳላሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም/ያለአግባብ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ መሰጠቱ ታውቋል፡፡

87. በተመሳሳይ መልኩ ኤም.ኤን.ኤስ የተባለ ድርጅት በቱርክ ባለሀብቶች የተቋቋመ የተቀናጀ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሲሆን በመመሪያው ላይ ፒክ አኘ እንጂ ላንድ ኩሩዘር የማይፈቀድ ቢሆንም አንድ ላንድ ክሩዘር መኪና ከጉምሩክ ታክስ እና ቀረጥ ነፃ ያስገባ መሆኑ ታውቋል፡፡

88. ኢ.ኤም ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/ የተባለው ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ ወተት እና የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበሪያ ፕሮጀክት ለማቋቋም በቀን 17/12/96 ዓ.ም በቁጥር አ.አ.ፈ0931/96 የተመዘገበ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተሰጠው ሲሆን ድርጅቱ በቀን 30/06/2007 ዓ.ም በቁጥር 01/01/1555/2015 ለኢንቨስትመንት ቦርድ በፃፈው ደብዳቤ ወተትና የወትት ውጤቶችን ለማጓጓዣ የሚውል ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እንዲችል ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱ የሙከራ ምርት ለመጀመር ግንባታውን አጠናቆ የማሽን ተከላ ለማድረግ በሒደት ላይ በመሆኑና የማቀዝቀዣ ክፍል ለመገንባት የማቀዝቀዣ እቃዎች በጅቡቲ ወደብ ላይ በመጓጓዝ ላይ ስለሆኑ በተጨማሪም ድርጅቱ የሊዝ ባለይዞታነቱ እስከ 12/08/2007 በስሙ ያልተዘዋወረ መሆኑ ነገር ግን ተሽከርካሪውን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ በቦርዱ መፈቀዱና ማስገባቱ ታውቋል፡፡

89. Hui chen የተባለ በ Electric bicycle assembling የስራ መስክ ተሰማርቶ የነበረ በቻይና ባለሀብት የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ድርጅቱ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 08 2015 ዓ.ም. የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት ሲሆን ድርጅቱ ህጉ ከሚፈቅድለት ውጭ 8 sino truck, 21 dumpers, 7 Toyota hilux , 2 tractors, 1 crane እና 1 ውሀ የሚረጭ መኪና ከቀረጥ ነፃ ማስገባቱ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

90. ለአበባ ኘሮጀክት አንድ ፒክ አኘ ቢፈቀድም ሼር ኢትዮጵያ የተባለ ድርጅት በአበባ ምርት ኢንቨስትመንት የተሰማራ ሲሆን ድርጅቱ ለሥራው ከሚያስፈልገው አንድ ሽፍን መኪና ለሥራ አስኪያጅና አንድ ትራክተር ከቀረጥ ነፃ ያስገባ መሆኑና እንዲሁም በቦርዱ ተፈቅዶለት 2 ኮልድ ትራኮችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባቱ ከኮሚሽኑ በተገኘና በተከለሰ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. በተጨማሪም በአማራ ክልል በባህር ዳር ከተማ ፀጋዬ ንጉሴ/ራዲያን ት/ቤት/ የተባለ በማህበራዊ የስራ ዘርፍ የተሰማራ ባለሀብት ሲሆን በዘርፉ ተሽከርካሪ በተሽከርካሪ መመሪያው ላይ የሚፈቅድ ባይሆንም 2 ሚኒባስ፣1 ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪ፣ 1ፒካፕ መኪና፡ 2 ሞተር ሳይክል ከቀረጥ ነፃ ማስገባቱ ከተከለሰ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. የኦዲት ቡድኑ በኮሚሽኑ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ ተሽከርካሪዎቹን ከመመሪያ ውጭ ላለመፍቀድ እየጣሩ እንዳሉ ነገር ግን በቦርዱ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በመኖራቸው በሳቸው መመለስ እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡

93. አብዛኛው ተሽከርካሪ የተፈቀደው በቦርዱ መሆኑን የኦዲት ቡድኑም ከከለሰው መረጃ ያረጋገጠ ሲሆን ቦርዱ በአዋጅ 269/2004 በአንቀጽ 29 ቁጥር 6 ላይ ደንቡ ከሚፈቅደው የተለየ ወይም በተጨማሪ አስፈላጊ ሲሆን ለምክር ቤት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል ቢልም ቦርዱ ከደንብና መመሪያ ውጭ በራሱ በመወሰን እየፈቀደ መሆኑ ከአዋጁ ጋር የሚጣረስ ሥራ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

94. ኮሚሽኑ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጠው መልስ ኤም.ኤን.ኤስ የተባለ ድርጅት ከፍተኛ የኤክስፖርት ኢንቨስትመንት በአጭር ጊዜ ተግባራዊ በማድረጉ በቦርዱ የተወሰነ መሆኑን፣ ኤስ.ደብልዩ.ኤስ የተባለ ድርጅት ከ24 በላይ ፋብሪካ የሚገነባ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ በመሆኑና አልሚዎች የተለየ የማበረታቻ ሥርዓት ያላቸው በመሆኑ እንዲሁም ኢ.ኤም ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ አስመልክቶ ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ተሽከርካሪ እንደ ካፒታል ዕቃ እንዲታይ ቦርዱ መወሰኑን ሼር ኢትዮጵያ የተባለ ድርጅት ትልቁ የአበባ እርሻ ልማት ያለው በመሆኑና የአገሪቱ 60 ከመቶ የአበባ ኤክስፖርት የሚያደርግ በመሆኑ የተፈቀደለት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

95. ይሁን እንጂ ኤስ.ደብልዩ.ኤስ የተባለው ድርጅት በግንቦት 30 ቀን 2007 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር ቀ/ነ/F2/112662/370 በተጻፈ ደብዳቤ በግልጽ ለጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ (General construction Grade one)አገልግሎት የሚውል በሚል ያስቀመጠ በመሆኑና ኢ.ኤም ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/ በኦዲት ሪፖርቱ የሊዝ ባለይዞታነቱ ሳይረጋገጥ መስጠቱን በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ የሌለ ሲሆን እንዲሁም ኤም.ኤን.ኤስ ድርጅትን አስመልክቶ ከፍተኛ የኤክስፖርት ኢንቨስትመንት በአጭር ጊዜ ማድረጉ ቢገለጽም በህዳር 12 ቀን 2007 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር 02.1.6/67 የኢትዮጵያ ጨርቃ

ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለኮሚሽኑ በጻፈው ደብዳቤ ምርቱን አገር ውስጥ በመሸጥ ላይ ካሉ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ መሆኑንና ለመንግሥት በገባው ቃል መሠረት ወደ ኤክስፖርት ትኩረት እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ቢያደርጉም የኤክስፖርት አፈፃፀም ሊያሻሽሉ ካልቻሉ ድርጅቶች አንዱ መሆኑን ገልጾ የጻፈ በመሆኑ ኮሚሽኑ የሰጠው ምክንያት ከኢንስቲትዮቱ ደብዳቤ ጋር የሚቃረን መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ በደንቡ በመሠረት መፈቀዱን በተመለከተ</u>፤

96. የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ባለሀብት በደንብ ቁጥር 270/2005 ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ሊፈቀድለት፣ አስፈላጊውን መረጃ አግባብ ላለው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሊያቀርብና እንዲሁም ከገቢ ግብር ነፃ በሆነበት ዘመን የሚያገኘውን ገቢ አግባብ ላለው የገቢ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

97. ማንኛውም ባለሀብት ቢያንስ 60 በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጪ ለሚልክ ባለሀብት በደንብ ቁጥር 270/2005 ባለው ሰንጠረዥ ከተፈቀደለት በተጨማሪ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ ሊሆን ይገባል፡፡

98. ሆኖም በናሙና በታዩት ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና የገቢ መ/ቤቶች ነፃ ገቢ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ ባለሀብቶች የተደራጀ መረጃ የሌለ፣ መረጃው ባለመኖሩም መረጃን መሠረት ያደረገ ጠንካራ የክትትል ሥርዓት አለመኖርና በመመሪያ የተሰጠና በትክክል ተጠያቂ የሆነ አካል የሌለ እንዲሁም ፍቃዱን የሚሰጡና የሚያስፈጽሙ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ግብር ከፋይ በተገኘ መረጃ የነፃ ገቢ ግብር የሚፈቅዱት አካላት በአድራሻ መላክ ሲገባቸው ግብር ከፋዩ እራሱ መረጃውን የሚያመጣበት አሠራር መኖርና አንዳንድ ባለሀብቶች በኦዲት አለመክፈላቸው ሲረጋገጥና ግብሩን እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ብቻ መረጃውን የሚያመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ቢሮዎች የገቢ ግብር ማበረታቻውን ተጠቃሚ የሆኑ ባለሀብቶች ማበረታቻውን እንዲያገኙ በአንድ ደብዳቤ የሚልኩና የተሟላ መረጃ /ድርጅቱ የት እንዳለ፣ መቼ እንደጀመር ምን ላይ እንደተሰማራ.../ የማይላኩና

የባለሀብቱ መረጃ ፈቃጁ አካል ጋርም በተሟላ መልኩ የማይገኝ በመሆኑ ጠይቀውም ማግኘት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

100. በተጨማሪም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች እስከ እዚህ ጊዜ የነፃ ግብር ተጠቃሚ ነው ብሎ መላክ ሲኖርባቸው በደፈናው በመመሪያ መሰረት ይፈጸም በሚል ደብዳቤ የሚልኩ በመሆኑ ለአሠራር ክፍተት መፈጠሩና ነፃ የገቢ ግብር ተጠቃሚ መሆን ከሚገባቸው አመት በላይ ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለሀብቶች መኖራቸውን ለምሳሌ ኖያ የተባለ ድርጅት ለአብነት የሚገለጽ ሲሆን የነፃ ገቢ ግብር ጊዜው ካበቃ በኋላ ለአንድ አመት ያልከፈለና በኢንቨስትጌሽን ኦዲት የተገኘ ሲሆን ያለአግባብ ተጠቃሚ የሆኑ ባለሀብቶች ለመቅጣት የወጣ ህግ አለመኖሩም ታውቋል፡፡፣ በሌላ መልኩ አንዳንድ በታክስ ኦዲት የገቢ ግብር ያልከፈሉ ባለሀብቶች ሲገኙና እንዲከፍሉ ሲጠየቁ አሁን ላይ ቆመው ወደ ኋላ ሄደው የመብት ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ ከኢንቨስትመንት ቢሮዎች የሚያመጡ መሆኑና በእነሱ አመለካከት መብት መታሰብ ያለበት ወደፊት መሆኑን፣ ሥራዉ ባለቤት የሌለውና ተጠያቂ የሚሆን አካል ሊኖር እንደሚገባው በኦዲቱ ወቅት አስረድተዋል፡፡

101. በባህር ዳር የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የባህርዳር ቅርንጫፍ በተገኘ መረጃ በአዋጁ ላይ 80 ፐርሰንት የሚሆነውን ምርቱን ወደ ውጪ የሚልክ ተጨማሪ የገቢ ግብር እፎይታ የሚያገኝ መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም ድርጅቱ ምን ያህል እንዳመረተ እና ምን ያህሉን ወደ ውጪ እንደላከ በሚመለከተው አካል ቁጥጥር እየተደረገ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን የገቢ ግብር ማበረታቻ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የሚያልቅበትን /መቼ እንደሚጨርሱ/ ባለሀብቶቹ እራሳቸው መጥተው ካላሳወቋቸው የመከታተያ ሥርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ እንዲሁም የነፃ ገቢ ግብር ማበረታቻ ተሰጥቷቸውና ጊዜያቸውን ጨርሰው ምንም የገቢ ግብር ከፍለው የማያውቁ እንደሀገር ጥቅም የማያስገኙ ድርጅቶች መኖራቸውን (ለምሳሌ አሸራፍ የተባለ ድርጅት) በተጨማሪም የእፎይታ ጊዜያቸው ሲያልቅ ስራቸውን ትተው የሚሄዱ ድርጅቶች መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

102. በተጨማሪም በባህርዳርና በመቀሌ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ በሆኑበት ዘመን የሚያገኙትን ገቢ የማያሳውቁ ባላህብቶች መኖራቸውን በጽ/ቤቶቹ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

103. በናሙና በታዩት በሁሉም የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና የገቢ መ/ቤቶች የገቢ ግብር ማበረታቻ በተመለከተ በባለቤትነት የሚያስተዳድር ተጠያቂ የሚሆን አካል /በግልጽ በመመሪያ የጸደቀ አለመኖርና የሚፈቅዱለት አካላት /የኢንቨስትመንት ቢሮዎች/ ጋር ሳይቀር የተደራጀ መረጃ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. ስለጉዳዩ በኮሚሽኑ የሚመለከታቸው ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው ነፃ የገቢ ግብር የድጋፍ ደብዳቤ መጻፍ የጀመሩት በቅርብ መሆኑና ንግድ ፍቃድ ለወሰዱ ድርጅቶች እየሰጡ የሚገኙ መሆኑንና ከዚህ በፊት ሥራውንም ሲሰሩ የነበሩት ገቢዎች እንደመሆናቸው ምን ያህል አመት መፈቀድ አለበት የሚለውንም መሥራት ያለባቸው እነሱ መሆናቸውን ነገር ግን በኃላፊነት ሥራውን ተቀብለው ሊሰሩት አለመቻላቸው፣ የኮሚሽኑ ሥራ ማበረታቻውን ማግኘት እንዳለበት ማሳወቅ ብቻ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በህግ የተሰጠ ነገር ባይኖርም ባለሀብት ከሚጉላላ በሚል ሥራውን እንደጀመሩት ገልጸዋል፡፡

105. ደንቡ 270/2005 አንቀጽ 9 ቁጥር 5 ነፃ የገቢ ግብር አስመልክቶ ተጠቃሚ ባለሀብቶች ተጠቃሚ የሚሆኑት አስፈላጊውን መረጃ አግባብ ላለው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ ነው ቢልም መረጃው እየቀረበ ያለው ለኢንቨስትመንት ቢሮዎች መሆኑና መሉ በሙሉ በባለቤትነት መሥራት ያለበትን አካል/ተጠያቂ የሚሆን/ በአዋጅ ወይም በደንብ የወጣ መመሪያ ባለመኖሩ ሥራው በተለያየ አካል እንደመሰራቱ ተናበው እየሰሩ አለመሆኑ ሥራው ላይ ከላይ የታዩ ክፍተቶች እንዲፈጠሩ ሆኗል፡፡

ለ. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጥር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጓቸውን ዕቃዎች
<u>ዝርዝር በቅድሚያ በማቅረብ እንዲያስፈቅዱ መድረጉን በተመለከተ</u>፤

106. ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከተው የኢንቨስትመንት አካል በቅድሚያ በማቅረብ ሊያስፈቅድ ይገባል፡፡

107. በደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ቁጥር 1 ላይ ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጋቸው የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከተው የኢንቨስትመንት አካል በቅድሚያ በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል ቢልም በናሙና በታዩት በትግራይ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል፣ በአዲስ አበባ፣ በአክሱምና ባህርዳር ከተሞች በሚገኙ የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ባለሀብቱ በቅድሚያ የቀረጥ ነፃ የሚያስገባቸውን የዕቃዎች ዝርዝር አቅርቦ እንዲያስፈቅድ አይደረግም፡፡

108. በኦዲቱ ወቅት በተሰበሰበ መረጃ ባለሀብቱ ዕቃዎችን ከገዛና የገዛበትን ኮሜርሽያል ኢንቮይስ፣ ፓኬጂንግ ሊስትና ቢልኦፍ ሎዲንግ የመሳሰሉት.... መረጃዎች እንዲያቀረብ በማድረግ የሚሰራ እንጂ አስቀድሞ የዕቃዎች ዝርዝር እንዲያቀረብ እንደማይደረግ የየመ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

109. ስለጉዳዩ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚመለከታቸው ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው ባለሀብቶች በመጀመሪያ በኮሚሽኑ ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ የማይደረግና የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲወሰዱም ያለምንም ጥናት በመሆኑ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲያወጡ ባለሀብቱ ዝርዝር እንዲያቀርብ ቢደረግም ዕቃው በተጨባጭ ባለሀብቱ የሚያውቀው ወደ ሥራ ሲገባ በመሆኑ አስቀድሞ እንዲያስፈቅድ እየተደረገ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

110. በመሆኑም ኮሚሽኑም ሆነ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች በደንቡ መሰረት ባለሀብቶች አስቀድመው ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የሚፈልጓቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያቀርብ አለመደረጉ ኢንቨስትመንት ቢሮዎቹ ባለሀብቶች በትክክል የሚያስፈልጋቸውን የዕቃ መጠን አይነት አውቀውና ያን መሠረት በማድረግ እየፈቀዱ አለመሆኑ ያለአግባብ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በር ሊከፍትላቸው የሚችል በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የነባር ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመፍቀድ አስቀድሞ የበፊት ኘሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ውጤታማነት መረጋገጡን በተመለከተ፤

111. የነባር ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመፍቀድ ኮሚሽኑ አስቀድሞ የበፊት ኘሮጀክቶች የኢንቨስትመንት አፈፃፀማቸውን ሊገመገም ይገባል፡፡

112. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል፣ በአክሱም፣ በአዲስ አበባና በባህርዳር ከተማ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች ነባር ለሆኑ ኘሮጀክቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ለመፍቀድ አስቀድሞ የነበረው አፈፃፀማቸው እንደማይገመገም ለማወቅ ተችሏል፡፡ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ለመስጠት የባለሀብቱን የቀድሞ አፈጻጸማቸውን ካለመገምገሙም በላይ አፈፃጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑን እያወቀም ማበረታቻውን እየሰጠ እንደሚገኝ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

113. ኢቱር ቴክስታይል ኃ.የተ.የግል ማህበር ምርቱን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ፣ ለምርት ሥራ የሚያገለግሉ ግብዓቶች ጨምሮ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻዎችን እንዲያገኝ የተደረገና በ2006 በጀት አመት 43,840,942.06 ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም ድርጅቱ ግን 17 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዕቅድ ውስጥ ብር 267,000 የአሜሪካን ዶላር /የዕቅዱን 1.6 በመቶ/ ብቻ ወደ ውጭ የላከ ሲሆን ነገር ግን ይህ ድርጅት በ2007 በጀት ዓመትም እስከ ህዳር ወር ድረስ ምንም ዕቃ ወደ ውጭ ባይልክም የቀረጥ ማበረታቻው ግን እስከ በጀት አመቱ መጨረሻ በኮሚሽኑ እንደተሰጠው ተረጋግጧል፡፡

114. ዶንግፋንግ የተባለ ድርጅት ጨርቃ ጨርቅ የሚሸምን የሚያጠናቅቅና የሚያመርት ድርጅት ሰኔ/2005 በቁጥር EIA-OL/3587/2014 የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የንግድ

ፍቃድ ያገኘ ሲሆን ኩባንያው ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት በየካቲት 2005 ዓ.ም. ከኢንቨስትመንት ቦርድ ጋር በተፈራረመው ውል መሰረት ለምርቱ በግብዓትነት የሚጠቀማቸውን ጥሬ እቃዎች ከቀረጥ ነፃ የማስገባት ልዩ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን ምርቱን ማምረት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በመጀመሪያው ዓመት 50 ፐርሰንት ምርቱን ወደ ውጪ መላክ (ኤክስፖርት) ማድረግ እንዳለበትና በየዓመቱ ወደ ውጪ የሚልከው የምርት መጠን ከፍ እያለ መሄድ እንዳለበት በውሉ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ፕሮጀክቱ ምርት ማምረት በመጀመር የንግድ ስራ ፈቃድ ከተሰጠው ከሰኔ 14 2006 ዓ.ም ጀምሮ በገባው ውል መሰረት ምርቱን ውጪ መላክ ያልጀመረና ከውሉ ውጭ ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ያለና ይህንን እስከ ታህሳስ 2007 ዓ.ም. ምንም ምርቱ ወደ ውጭ እንደማይልክ ኮሚሽኑ ቢያውቅም በ2006 ዓ.ም. ብር 103,316,903 (መቶ ሦስት ሚሊዮን ሦስት መቶ አስራ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሦስት ብር)ተጠቃሚ የሆነ ሲሆን እስከ 2007 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ አፈጻጸሙ እየታወቀ ብር 33,106,507 (ሰላሳ ሦስት ሚሊዮን መቶ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር)ድርጅቱ ከቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ እንዲሆን መደረጉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተገኘ መረጃ አሽራፍ በ17/6/96 የምግብ ዘይት፣ በ8/7/96 የሥጋና የጁስና የውሃ ምርቶችና በ16/7/96 የሥጋና አሳ ማቀነባበሪያ የሥራ ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ያወጣ ሲሆን የኢንቨስትመንት አዋጅ አንቀጽ 17 ቁጥር አራት ላይ ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፍቃድ ካወጣበት ጊዜ እስከ ሁለት አመት ትግበራውን ሳይጀምር ሁለት አመት ካለፈው የኢንቨስትመንት ፈቃዱ እንደሚሰረዝ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱ የሥጋ ምርቱን 7 አመት ቆይቶ በ2003 ዓ.ም. በይፋ ተመርቆ ወደ ምርት ተግባር የገባና በዚሁ አመት ወደ አንጎላና ኮሞሮስ ሥጋ መላክ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በዚሁ አመት መልሶ ማቋረጡ ታውቋል፡፡ እንዲሁም የዘይት ፋብሪካውም እስካሁን ወደ ምርት ያልገባ ሲሆን ያለፈው አፈጻጸሙ መገምገም ሲኖርበት በ2002 ዓ.ም. በድጋሚ ለኢንቨስትመንት ማስፋፊያ በሚል ለእንስሳት መኖ ማደራጃ ፋብሪካ፣ የስጋ ከብቶች ማደለቢያና ለኘላስቲ ፋብሪካ ፍቃድ የተሰጠው ሲሆን የስጋ ከብት ማደለቢያው በሙሉ አቅሙ እስከ 2007 ዓ.ም. ወደ ሥራ ያልገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ ድርጅቱ ከ10 ዓመት በላይ ወደ ሙሉ ምርት ተግባር ሳይሸጋገር መቆየቱን ተከትሎ የመሬት

ውል በ12/02/2006 ዓ.ም በአማራ ክልል ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ እና በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪ ልማትና ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በኩል እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ አፈፃፀሙን እያወቀ ከ2003-ግንቦት 2006 ብር 14,928,784 (አሥራ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ አራት ብር)ከቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፣

116. ስለጉዳዩ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ማስፈጸሚያ ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በነሱ በኩል የቀረጥ ማበረታቻውን ለመፍቀድ በአዋጁ መሰረት የታደሰ የኢንቨስትመንት ፍቃድ መኖሩን የንግድ ፍቃድ ካወጣ ወይም ነባር ድርጅት ከሆነ 50 ሰው መቅጠሩን የሚያዩና ይህን ካሟላ አዋጁ ስለሚፈቅድና መብቱም ስለሆነ የሚፈቅዱ መሆኑን ነገር ግን የሚከታተለው አካል ችግር አለበት ካለ ግን እንደሚያቆሙ ገልጸዋል፡፡

117. ባለሀብቱ ያለፈው አፈጻጸሙ ሳይታይ ወይም አፈጻጸሙ ዝቀተኛ መሆኑ እየታወቀ መፈቀዱ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን ለአገር ከሚሰጠው ፋይዳ አንጻር ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

118. ኮሚሽኑ በሪፖርቱ ላይ በሰጠው መልስ በኮሚሽኑ ደረጃ የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ችግር እንዳለባቸው ሪፖርት የሚያቀርብባቸው ፕሮጀክቶች/ድርጅቶች ሳይጣራ እንደማይስተናገዱና ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች የራሳቸው ማብራሪያ ያላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

119. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቶች የበፊት አፈጻጸማቸው የሚመገምበት አሰራር ስለመኖሩ የሚያሳይ ምንም አይነት ማስረጃ የሌለ ሲሆን ከላይ የተገለጹት ድርጅቶች የተለየ ማብራሪያ እንዳላቸው ቢገለጽም የተለየ ማብራሪያው ምን እንደሆነ ግልጽ አለመሆኑ እንዲሁም ከላይ የተገለጹት ድርጅቶች አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ቢሆንም በኮሚሽኑ የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ የተሰጣቸው መሆኑን ከተለያዩ መረጃዎች በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የወሰዱ ባለሀብቶች ማበረታቻዎችን ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ያለውን የክትትል ሥርዓትና ስለኢንቨስትመንታቸው <u>የአፈፃፀም ሂደት በየሦስት ወሩ ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ</u>፤

120. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ባለሀብት ስለኢንቨስትመንቱ የአፈፃፀም ሂደት በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊያደርግና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በሙሉ ዕቅድ አውጥቶ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

121. ይሁን እንጂ አብዛኛው ባለሀብት የአፈፃፀም ሪፖርት በየሦስት ወሩ እያቀረበ አይደለም እንዲሁም በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን የተሰጣቸው ባለሀብቶች ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ስለማዋላቸው ከአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በስተቀር በዕቅድ ተይዞ ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

122. በኦዲቱ ወቅት በተሰበሰበ መረጃ በናሙና በታዩት በአማራና ኦሮሚያ ክልል፣ በአዲስ አበባና ባህርዳር ከተሞች በሚገኙ የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተጠናከረ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ እራሱን የቻለ ክፍል አለመኖርና የሰው ኃይልና የተሽከርካሪ እጥረት በመኖሩ የሚካሄደው ክትትል የተጠናከረ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አልፎ አልፎ ትክክለኛ አድራሻ የማይሰጡና አድራሻቸው በትክክል የማይታወቅ ባለሀብቶች እንደሚያጋጥሙ ገልጸዋል፡፡ በአማራ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ ለመከታተል ግልፅ የሆነ አሰራር የሌለ መሆኑን፣ የካፒታል እቃዎች እና የግንባታ እቃዎች መጠን ገደብ ስለሌለው ለመቆጣጠር አስቸጋሪ መሆኑንና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ኪራይ ላይ ተንቀሳቃሽ ስለሆኑ ለመከታተል አስቸጋሪ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በኮንትራክሽን ዕቃዎች

ላይ ከ10,000 በላይ ለሆኑ ባለሀብቶች ስለተሰጠ ለመከታተል ስለሚያስቸግር እንደማይከታተሉ የሥራ ኃላፊዎቹ ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

124. በትግራይ ክልል አወቃቀሩም ቢሆን በሥራ ሂደት ደረጃ መሆኑና በሌሎች በክልሉ ባሉ ከተሞች የሚገኙ ቢሮዎች ከመቀሌ በስተቀር ሁለት ሠራተኛ ብቻ በመኖሩ ተገቢው ክትትል የማይደረግ መሆኑ አስረድተዋል፡፡

125. በተጨማሪም በትግራይ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን እንዲሁም የተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ድጋፍ የተደረገላቸው ድርጅቶች የማበረታቻው ተጠቃሚ መሆን አለመሆናቸውን የሚገልጽ ወቅታዊና የተደራጀ መረጃ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሊገኝ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ማበረታቻው ለታለመለት አላማ ማዋል አለማዋላቸው ለመከታተል ችግር መኖሩንና በሁሉም የኢንቨስትመንት ቢሮዎች የግንባታ ዕቃዎች ላይ/በተለይ ብረት/ ግንባታው ላይ በትክክል መዋሉን ለመቆጣጠር የአቅም ውሱንነት መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

126. በተጨማሪም ባለሀብቶች ሪፖርት በየሦስት ወር ማቅረባቸውን በተመለከተ በትግራይና በአክሱም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች አብዛኛው ባለሀብቶች በየሦስት ወሩ የአፈፃፀም ሪፖርት እያቀረቡ አለመሆኑና በየጊዜው ሪፖርት ባለማድረጋቸው የት እንዳሉና በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፣ በአማራ ኢንቨስትመን ቢሮ አብዛኛው ባለሀብት ሪፖርት እንደማያቀርብና አንዳንድ ባለሀብቶች ጉዳያቸውን /የቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን/ ለማስፈፀም ሲፈልጉ ብቻ ሪፖርት የሚፅፉ መሆኑ፣ በኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ በክልላቸው ባለሀብቱ ሪፖርት አድርገው የማያውቁ መሆኑ፣ በአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በተለይ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ባለሀብቱ ሪፖርት የማያደርግ መሆኑ፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ባለሀብቱ ጊዜውን ጠብቀው በየሦስት ወሩ የማያቀርቡና ጭራሽ ሪፖርት የማያደርጉ ፕሮጀክቶች መኖራቸው ሪፖርት የማያቀርቡትም በደንቡ ላይ ፍቃዳቸው ይሰረዛ ቢልም ፈቃዳቸውን የማይሰርዝ መሆኑ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ገልጸዋል፣

127. በኮሚሽኑ ከተከለሱ መረጃዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በ2007 ዓ.ም. የፕሮጀክቶችን ወርሃዊ እቅድ እና አፈፃፀም ማዕከል በማድረግ

ተከታታይነት ያለው የመስክ ምልከታ ያለመደረጉን፣ በጋምቤላ ባለሀብቶች የሚገኙባቸው ቦታ ላይ ተገኝቶ የፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ኤጀንሲው ምንም ተሽከርካሪ የሌለው መሆኑን፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ንግድ ሚኒስቴር ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ፕሮጀክቶችን ለመከታተል የባለሙያ አቅም ውስንነት መኖሩን፣ በግብርና ኢንቨስትመንት ስም የሚገኙ የማሽነሪና ሌሎች ድጋፎች ላልተፈቀደለት አላማ እንዲውል ማድረግና ይህም በተራው በልማት እቅድ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

128. በኢትዮጵያ ገቢዎች ባለሥልጣን የቃሊቲ ጉምሩክ ኃላፊዎችና ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኢንቨስትመንት ቢሮዎቹ የሰጡትን የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ እንደማይከታተሉና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የተፈቀዱ ዕቃዎች ቁጥጥር ስለሌለ ከቀረጥ ነፃ የገቡና ሥራ ላይ ያለው የተለያየ መሆኑን በዚህም ምክንያት ባለሀብቱ የወሰደውን ማበረታቻዎች ከታለመላት አላማ ውጭ እያዋሉ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ከመስከረም 2006 ዓ.ም. እስከ ህዳር 2008 ዓ.ም. ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ያስገቺዉን ተሽከርካሪዎች፣ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችና የመሳሰሉት ለሦስተኛ ወገን ያስተላለፉና ያለአግባብ ከታቀደላቸው አላማ ውጭ ያዋሉ 189 ባለሀብቶች በጥቆማና በተለያየ መንገድ መገኘታቸውን ከጉምሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ የገቢ፣ የተሰብሳቢና ዋስትና ሂሳቦች አስተዳደር ክፍል በተገኘ መረጃ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ገቢዎችና ጉምሩክ ባህርዳር ቅርንጫፍም በጥቆማና በተለያየ መንገድ የተለያዩ ተሽከርካሪዎችን በተመሳሳይ ለሦስተኛ ወገን ተላልፈውና ከታቀደለት አለማ ውጭ ውለው መገኘታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

129. በተጨማሪም በኮሚሽኑ አስፈላጊ ክትትል ባለመኖሩ ኢትዮ አግሪ ሴፍት የተባለ ድርጅት ሦስት የኢንቨስትመንት ፍቃዶች አውጥቶ ሲጠቀም የነበረ መሆኑ በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በ29/10/01ና በ5/6/2015 እንዲሁም በአማራ ክልል ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በ4/7/2001 አውጥቶ በአማራ ክልል ያወጣውን ኢንቨስትመንት ፈቃድ በቀን 12/09/07 የተዘጋ /የተሰረዘ/ ቢሆንም በሁለቱም ኢንቨስትመንት ፍቃድ ያለአግባብ ሲጠቀም የነበረና እስከ ሰኔ 2007 ዓ.ም. ድረስ ብር 43,892,361 የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ መሆኑን ከጉምሩክ የመረጃ ቋት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን

በተጨማሪም ያለንግድ ፍቃድ ምርቱን እየሸጠም የሚገኝ ድርጅት መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

130. በመሆኑም የኢንቨስትመንት ቢሮዎቹ ዕቅድ አውጥተው የሰጡትን ማበረታቻ ለተቀደለት አላማ መዋሉን አለመከታተላቸው አገሪቷ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ባለሀብቶች ያለአግባብ እንዲጠቀሙበት የሚያደርግና የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ አሰጣጥ አላማንም የተዛባ የሚያደርግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባለሀብቱ የተሰጠውን ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ አውለው ሲገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሰርዙንና ከተሰረዘበት ቀን <u>ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ መደረጉን በተመለከተ</u>፤

131. የኢንቨስትመን አዋጅ 769/2004 አንቀጽ 19 ቁጥር 2 እና 4 በኮሚሽኑ ፍቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች በኮሚሽኑ፣ የተሰጡ ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ውለው ወይም ከህግ ውጪ ለሌላ ሰው ተላልፈው ከተገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊሰርዝ ይገባል፡፡ እንዲሁም ያገኟቸውን ጥቅሞች ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች አካላት ተመላሽ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

132. ይሁን እንጂ በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን የተሰጣቸው ባለሀብቶች ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ስለማዋላቸው ያለው ክትትል የላለ በመሆኑ ባለሀብቶች የወሰዱት ዕቃዎች በትክክል ለተፈቀደለት አለማ ያውሉት ወይም አያውሉት የማያውቁና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 279 በአንቀጽ 19 ቁጥር 3 መሠረት በተለያየ ምክንያት ኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰረዘባቸውን ባለሀብቶች ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል ቢልም በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎችም ሆኑ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ፍቃዳቸው የተሰረዘና የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ ባለሀብቶችን ለይተው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንደማያሳውቁ በኦዲቱ ወቅት ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ኃላፊዎች በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከታቀደለት አላማ ውጭ አውለው የተገኙ

ባለሀብቶች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ እንዲያደርጉ እንደማይደረግ በኮሚሽኑ ከተገኙና ከተለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

133. በተጨማሪም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በደንቡ መሠረት ባለሀብቶች ከታቀደላቸው አላማ ውጭ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን ሲያውሉ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲከፍሉ የማይደረግና በመመሪያ ቁጥር 69/2004 በቅድሚያ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ 25 በመቶ ከፍሎ ቀሪውን ክፍያ /75 በመቶ/ በሁለት አመት ጊዜ ውል በመዋዋል መከፈል እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን በአሁን ወቅት ከዋናው መ/ቤት በተላከ መመሪያ በአራት አመት ጊዜ ውስጥ እንዲከፍሉ እየተደረገ ያለ ሲሆን ከ2006 ዓ.ም. እስከ ህዳር 2008 ዓ.ም. የቀረጥ ማበረታቻውን ለሌላ አላማ ሲያውሉ የተገኙና ለመክፈል ስምምነት ከገቡት 189 ባለሀብቶች ውስጥ 48 ክፍያውን ያልፈጸሙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 44ቱ የቦንድ ጊዜያቸው/የመክፈያ ጊዜያቸው/ ያበቃ መሆኑ አራቱም ሙሉ በሙሉ ክፍያውን ያልጀመሩ /ብር 13,883,315.7/ የቦንድ ጊዜያቸው/የመክፈያ ጊዜያቸው/ ያላበቃ ሲሆን 16ቱ ደግሞ የአንድ ጊዜ ክፍያ ብቻ 25 በመቶውን ከፍለው /ያልተከፈለ ብር 6,211,824.74/ ሳይከፍሉ ያቋረጡ መሆኑን ከጉምሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ የገቢ፣ የተሰብሳቢና ዋስትና ሂሳቦች አስተዳደር ክፍል በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

134. ስለጉዳዩ በጉምሩክ አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ህግ ማስከበር ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እነዚህ 64 ድርጅቶች አዋጅ 622/2006 አንቀጽ 98/2-ለ ላይ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻን ከተሰጠበት አላማ ውጭ ለሌላ አገልግሎት ያዋለ ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ ሰው ዕቃው በገባ ጊዜ ሊከፍል የሚገባው ታክስ የሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከሦስት እስከ አምስት አመት የሚደርስ እስራት ይቀጣል የሚልና እንደ ወንጀልም ይቆጠር የነበረ ሲሆን በአዲሱ ማለትም በህዳር 2007 የተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 ቁጥር 1 ላይ ግን የቀረጥና ታክሱን 50 በመቶ ብቻ ገንዘብ ይቀጣል የሚል በመሆኑ ቅጣታቸውን ባለመክፈላቸው እርምጃ ለመውሰድ አለመቻሉን /ማስገደድ የማይቻል መሆኑን/ በተጨማሪም ቅጣቱ አስተማሪ ካለመሆኑም በላይ ወደዚህ ማጭበርበር እንዲገቡ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ክፍተት እንዳለው ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን

የሚቆጣጠር ወይም የሚከታተል አካል ስለሌለና በደንቡ መሠረት የተሰረዙ ባለሀብቶች በተከታታይ የማይላኩ በመሆኑ ጥቆማዎች መሠረት በማድረግ እርምጃ የሚወሰዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

135. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መቀሌ ቅርንጫፍ በተገኘ መረጃ በትግራይ ክልል ወደ 70 የሚሆኑ ባለሀብቶች ሆቴል እንገነባለን በሚል ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም. ግንባታው ከሚፈለገው በላይ ቢል ኦፍ ኮንቲቲ በማሰራት ባጠቃላይ ወደ ብር 311,841,873.87 ያለአግባብ ከቀረጥ ነፃ ያስገቡ ቢሆንም ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል።

136. እንዲሁም ከአማራ ክልል በተገኘ መረጃ አሽራፍ የተባለ ድርጅት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከ1996 ጀምሮ ፍቃድ የተሰጠው ድርጅት ሲሆን በግንባታ ዕቃ ኪራይ የመጣ ተሽከርካሪ ለሌላ አገልግሎት ሲውል ተገኝቶ የተወረሰበት እና እስከ ጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም. ተወርሶ በባህር ዳር ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጊቢ ውስጥ ቆሞ የሚገኝ ቢሆንም ይህ ድርጅት ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ፍቃዱ ያልተሰረዘበት መሆኑ፣ በተጨማሪም ዶንግፋንግ የተባለ ድርጅት ምርቱን ማምረት ከጀመረበት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ 50 በመቶ ውጭ ሊልክ ውል የተዋዋለና በአገር ውስጥ እየሸጠ መሆኑ ቢደረስበትም በኮሚሽኑ እርምጃ የተወሰደ አለመሆኑ፣ ካራቶሪ የተባለ ድርጅት ተረክቦ በግብርና ኢንቨስትመንት ልማት ላይ የተሰማራ ሲሆን ለልማቱ አስፈላጊ የሆኑ በርካታ የማሽነሪ መሳሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ ያስገባ ቢሆንም አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ከታሰበው አላማ ውጭ ለሌሎች ባለሀብቶች እያከራየ እንደሚጠቀም በ2006 ዓ.ም የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳዳሪ ኤጀንሲ ባለሙያዎች ለመሬት አጠቃቀም ግምገማ ወደ መስክ የተንቀሳቀሰ የባለሙያ ቡድን ያረጋገጠ ቢሆንም እስከ ታህሳስ 2007 ዓ.ም. ያልተሰረዘ መሆኑንና ከ2003-2005 ዓ.ም. ብቻ 157,108,478 ብር ከቀረጥ ነፃ ያስገባና ታህሳስ 2007 ዓ.ም. የኢንቨስትመንት ፍቃዱ የተሰረዘበት ቢሆንም /የኦዲት ቡድኑ ባለው መረጃ ነው ከዛ በፊትም ወስዶ ሊሆን ይችላል/ብሩን ተመላሽ ያደረገ ስለመሆኑ በኮሚሽኑም ሆነ በገቢዎች መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

137. Hui chen የተባለ በElectric bicycle assembling የስራ መስክ ተሰማርቶ የነበረ ድርጅት ሲሆን ድርጅቱ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 08/2015 የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት ሲሆን ተሽከርካሪን፣ የካፒታል እቃዎችን እና መለዋወጫዎችን ጨምሮ 42,384,949.58 ያህል ብር ከቀረጥ ነፃ ቢደረግም ከቀረጥ ነፃ ያስገባቸውን ተሽከርካሪን እና የካፒታል እቃዎችን ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

138. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊ ተጠይቀው በኮሚሽኑ በኩል የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ ተለይቶም ባይሆን የተሰረዙ ባለሀብቶችን አስፈላጊው ይፈጸም በሚል ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ የሚልኩ መሆኑን ለወደፊት አስፈላጊ ከሆነ በግልባጭ ሥራውን ለሚሰራው ክፍል /ቃሊቲ ቅርንጫፍ የህግ ማስከበር/ እንደሚልኩና አንዳንድ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ካራቶሪን የመሳሰሉ በመንግሥት ደረጃ መያዛቸውን ገልጸዋል፡፡

139. ሆኖም በኮሚሽኑ የኮንትራት አስተዳደር ክፍል የተሰረዙና የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የወሰዱ ባለሀብቶች ለማስመለስ ክትትል የማይደረግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህ ደግሞ ሥራው ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት አለመሆኑን የሚያሳይና የቀረጥ ነፃውን ያለአግባብ የሚጠቀሙ ባለሀብቶችንም የሚያበረታታ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

140. ኮሚሽኑ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ መልስ በሰጠው ምላሽ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲሰረዝ ለገቢዎችና ጉምሩክ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ እንደሚላክና አሰራሩም የተለመደ መሆኑን ገልጿል፡፡

141. ደብዳቤው እንደሚላክ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም ደብዳቤው ሲላክ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የወሰዱ ባለሀብቶች በግልጽ የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ስለመውሰዳቸው ተገልጾ ሳይሆን ማበረታቻውን የወሰዱ ሆኑ ያልወሰዱ ባለሀብቶች ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ በሚል የሚላክ መሆኑን ከማስረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርና በማበረታቻ አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ ውይይት መኖሩን በተመለከተ፤

142. ኮሚሽኑ በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር በማመቻቸት በቅንጅት ሊሰራና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ከባለሀብቶች ጋር በኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ የመወያያ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

143. በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ኮሚሽኑ በናሙና በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል፣ በአክሱም፣ በአዲስ አበባና በባህርዳር ከተማ የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ገቢዎች ባለሥልጣን የመቀሌ፣ የባህርዳርና አዲስ አበባ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች በየሦስት/በየስድስት ወሩ ግምገማ ከሚደረገው ውጭ በሥራው ላይ ጠንካራ የሆነ የሥራ ግንኙነት የሌላቸው፣ ልምድ ልውውጥ የማያደርጉ፣ ድጋፍና ሥልጠናም የማያገኙ፣ ህግ ሲወጣም የማይወያዩና አዳዲስ ነገሮች ሲመጡ ቶሎ የማይደርሳቸው በመሆኑ ሥራቸው ላይ ግልጽ ያልሆነ ነገር ሲኖር /የህግ ማብራሪያ ሲፈልጉ በደብዳቤ እየጠየቁና እየሰሩ ያሉ መሆኑ እንዲሁም ኮሚሽኑ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ባለሀብቶችንም ሆነ የባለድርሻ አካላትን የሚያወያይበት ወጥ የሆነ የውይይት መድረክ የማያዘጋጅ እንዲሁም በአዋጁ፣ በደንቡ፣ እና በመመሪያዎች ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ ለመጨመር የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱንና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የቀረጥ ነፃ ማስተባበሪያ የሚመለከታቸው ኃላፊ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ጋር የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት የሌለ መሆኑና የገቢዎችና የኮሚሽኑ የሥራ ድርሻ በግልጽ የተቀመጠም አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

144. በተጨማሪም ከተከለሱ መረጃዎች በየክልሉ ያሉት ዘርፉን ለመደገፍ የተቋቋሙት ተቋማት (ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ግብርና፣ የአካባቢ ጥበቃ እና መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የመሳሰሉት) እርስ በርሳቸው እንዲሁም በፌዴራል ከሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው መስራት አለመቻላቸው እና በኃላፊነት ዘርፉን ያለመደገፍ ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

145. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የሚመለከታቸው ኃላፊ ተጠይቀው የጉምሩክ ቀረጥ ቴክኒካል እና ስቲሪንግ ኮሚቴ ላይ ገቢዎች ሰብሳቢ ሆኖ እንደሚሰሩና ገቢዎች ላይ በየሁለት ሳምንት እንደሚነጋገሩ ገልጸዋል፡፡

146. ሆኖም በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና ከገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር የታዩት ክፍተቶች ያለውን የሥራ ግንኙነት የላላ መሆኑን የሚያሳይና በሥራውም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሐ. <u>በኮሚሽኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ</u>፤

147. ኮሚሽኑ አገልግሎቱን በቅልጥፍናና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡

148. በኦዲቱ ወቅት በትግራይ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል፣ በአዲስ አበባ፣ በአክሱምና ባህርዳር ከተማ ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በመቀሌ፣ ባህርዳርና አዲስ አበባ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት የሌለ መሆኑ፣ ለባለሀብቶች የቀረጥ ነጻ ማበረታቻውን ድጋፍ የሚጽፈውና ፍቃድ የሚሰጠው አካል የተለያየ እንደመሆኑ ኔትወርክድ የሆነ አሠራር ባለመኖሩ ድጋፍ የጻፉለት ባለሀብት በትክክል ማበረታቻውን ስለመውሰዱ መረጃውን በቀላሉ ማግኘት አለመቻላቸው ወይም እንዲያውቁ አለመሆኑ፣ የባህርዳርና የአማራ ክልል ኢንቨስትመን ቢሮዎች ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶችን መረጃ በሲዲ የሚለዋወጡ መሆኑና በአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ኢንተርኔ በራሱ የገባላቸው በህዳር 2008 ዓ.ም. መሆኑን ገልጸዋል፡፡

149. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ ኃላፊ ሲገልጹ መረጃ የሚይዙት እንደነገሩ መሆኑንና ኮምፒውተሮቻቸው በቫይረስ በመሳሰሉት ቢጠቃ መረጃዎች የተጠበቁ እንዳልሆኑ፣ ኢንተርኔት በመ/ቤቱ ቢኖርም የኢንፎርሜሽን ስርዓቱን ለማጠናከር በኮሚሽኑ እየተሰራ አለመሆኑ በገቢዎች ግን ጅምር ስራ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

150. በተጨማሪም ከኮሚሽኑ በተገኝና በተከለሰ መረጃ የውጭ ባለሀብቶች መረጃዎች ጥራት ማነስና የክልል መረጃዎችም ተሟልቶ አለመገኘቱ፣ የሪከርድና ማህደር

ፋይሎች በተገቢው መንገድ አለመደራጀታቸው፣ የተፈጠሩ የሥራ እድሎች መረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ አለመደረጉ የፕሮጀክቶች የአፈፃፀም ደረጃ መረጃዎች በአግባቡ አለመያዛቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ በሥራ ላይ እያለ የመዝገብ ክፍሉ ጠባብ በመሆኑና የባለሀብቶች ፋይሎች ጥራዝ ብዙ እንደመሆኑ በቂ መደርደሪያዎች የሌሉትና የመዝገብ ቤት ሰራተኞች እንደልብ መዘዋወርና በቀላሉ ለማውጣት አስቸጋሪ የሆነና ፋይሎችም የመቀዳድ ሁኔታ መኖሩን በአካል ምልከታ ማረጋገጥ ችሏል፡፡

151. እንዲሁም ኮሚሽኑ ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ መደበኛ እና ተከታታይ የሥራ አመራር ውይይት የሌለውና በ2007 አራት ጊዜ ብቻ ማድረጉን እንዲሁም የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ በአመቱ ውስጥ አለማድረጉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

152. በመሆኑም ጠንካራ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ባለመኖሩ የኢንቨስትመንት ቢሮዎቹም ሆኑ የገቢ መ/ቤቶች ያለውን መረጃ በቀላሉ እንዳይለዋወጡ በማድረጉ ክትትል ላይ ክፍተት የሚፈጥር መሆኑ በተጨማሪም ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ የሆነ የውይይት መድረክ አለመኖሩና ቦርዱም በደንብ 313/2006 መሰረት በየወሩ አለመሰብሰቡ ከቀረጥ ነጻ ማበረታቻው ላይ የሚገኙ ችግሮችን ለበላይ አመራሩና ለቦርዱ ቀርበው መፍትሄ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

ክፍል ሦስት

መደመደሚያ

153. **በኮሚሽኑ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከባለሃብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ጥያቄ የቀረቡ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

- በኮሚሽኑ መውጣት ሲገባቸው ያልወጡ መመሪያዎች መኖራቸውና /የካፒታል ዕቃ ዝርዝር መመሪያ አለመውጣቱ፣ የግንባታ ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃዎች በመጠን የተቀመጠ ህግ አለመኖሩ/ የማየተገበሩ መመሪያና ደንቦች መኖራቸው፣
- ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለሚሰጣቸውና የቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን ለሚፈቅድላቸው ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡ አያደርግም እንዲሁም ባለሀብቶች ያላቸውን የፋይናንስና የሰው ኃይል አቅም አይገመገምም፡፡
- በናሙና በታዩት በትግራይ፣ በአማራና በኦሮሚያ እንዲሁም በአክሱም፣ በባህርዳርና በአዲስ አበባ የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች ለፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው መሆናቸው ሳይረጋገጥ እንዲሁም ደንቡ ከሚያዘው ውጭ አላግባብ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕቃዎችና አክሰሴሪዎች መኖራቸው፡፡

- በናሙና በታዩት ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና የገቢ መ/ቤቶች ነፃ ገቢ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ ባለሀብቶች የሚፈጽመው አካል የሚፈቅደው አካል /ተጠያቂ የሆነ/ በመመሪያ ጥርት ብሎ የወረደ ነገረ አለመኖሩ፣ የተደራጀ መረጃ የሌለና መረጃው ባለመኖሩም መረጃን መሠረት ያደረገ ጠንካራ የክትትል ሥርዓት የሌለ፣ ፍቃዱን የሚሰጡና የሚያስፈጽሙ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት አለመኖሩ፣
- ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር 269/2004 አንቀጽ 29 ቁጥር 6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሥራ ላይ ባለው ደንብ መሠረት ከሚፈቀደው የተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፈቀድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል ቢልም አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ በራሱ እየፈቀደ የሚገኝ መሆኑ፣
- ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን መጋቢት 2005 ዓ.ም. ከወጣው መመሪያ ውጭ የኢንቨስትመንት የሥራ አመራር ቦርድ እየፈቀደ መገኘቱ፣
- በደንብ ቁጥር 270/2005 ላይ የካፒታል ዕቃ ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የማምረቻ መሣሪያዎች መሆኑን የሚገልጽ ቢሆንም በናሙና የታዩት ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ኮሚሽኑም ሆኑ የሥራ አመራር ቦርዱ ድርጅቶች ከሚያመርቱት ምርት ወይም ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ዕቃዎች እየፈቀዱ የሚገኙ መሆኑ ለምሳሌ /የቤት ቁሳቁሶች፣ የቢሮ ፈርኒቸሮች፣ የኤሌትሪክ ዕቃዎች እንደካፒታል ዕቃ በመቁጠር፣ ጀነሬተሮች፣ የሰራተኛ ሰዓት መቆጣጠሪያ ማሽኖች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ ካሜራዎች……/
- በደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ አስራ አንድ ቁጥር አንድ ላይ ማንኛውም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል የሚል ቢሆንም ድርጅቶች የማስፋፊያ ሥራ ሳይኖራቸው ማምረት ከጀመሩም በኋላ የካፒታል ዕቃዎች እየተፈቀዱ የሚገኙ መሆኑ፣
- በኮሚሽኑ/በሥራ አመራር ቦርዱ የመለዋወጫ ዕቃዎች ደንቡ ድርጅቶች ማምረት ከጀመረበት ጊዜ እስከ አምስት አመት እንደሚፈቀድላቸው የደነገገ

ቢሆንም ከደንቡ ውጭ ማምረት ሳይጀምሩና ማምረት ከጀመሩት አምስት አመት በኋላ የሚፈቀድላቸው ድርጅቶች መኖራቸው፡፡

154. **ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤**

- በትግራይ፣ አማራና በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በአክሱም፣ በባህርዳርና በአዲስ አበባ ከተማ የኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ባለሀብቶች ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈልጓቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከተው የኢንቨስትመንት አካል በቅድሚያ በማቅረብ እንዲያስፈቅዱ አይደረገም፡፡
- በናሙና በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል፣ በአክሱም፣ በአዲስ አበባና በባህርዳር ከተማ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች ነባር ለሆኑ ፕሮጀክቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ለመፍቀድ አስቀድሞ የነበረው አፈፃፀማቸው አይታይም፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ለመስጠት የባለሀብቱን የቀድሞ አፈጻጸማቸውን ካለመገምገሙም በላይ አፈፃጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑን እያወቀም ማበረታቻውን እየሰጠ ይገኛል፡፡
- በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች አብዛኛው ባለሀብት የአፈፃፀም ሪፖርት በየሦስት ወሩ እያቀረበ አይደለም እንዲሁም ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን የተሰጣቸው ባለሀብቶች ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ስለማዋላቸው በዕቅድ ተይዞ ክትትል እየተደረገ አይደለም፡፡
- በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻውን የተሰጣቸው ባለሀብቶች ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ስለማዋላቸው ያለው ክትትል የላላ በመሆኑ ባለሀብቶች የወሰዱት ዕቃዎች በትክክል ለተፈቀደለት አለማ ያውሉት ወይም አያውሉት የማያውቁና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 279 በአንቀጽ 19 ቁጥር

3 መሠረት በተለያየ ምክንያት ኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰረዘባቸውን ባለሀብቶች ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል ቢልም በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎችም ሆኑ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ፍቃዳቸው የተሰረዘና የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ ባለሀብቶችን ለይተው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አያሳውቁም፡፡ የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከታቀደለት አላማ ውጭ የሚያውሉ ባለሀብቶች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ እንዲያደርጉ አይደረግም፡፡

- በተጨማሪም ከተከለሱ መረጃዎች በየክልሉ ያሉት ዘርፉን ለመደገፍ የተቋቋሙት ተቋማት (ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ግብርና፣ የአካባቢ ጥበቃ እና መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ እና የመሳሰሉት) እርስ በርሳቸው እንዲሁም በፌዴራል ከሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው መስራት አለመቻላቸው እና በኃላፊነት ዘርፉን ያለመደገፍ ሁኔታ መኖሩን፣ በኮሚሽኑና በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች መካከል ጠንካራ የሆነ የሥራ ግንኙነት አለመኖሩ በሚፈለገው ደረጃ ኮሚሽኑ ቢሮዎችን አለመደገፉ፣ በኮሚሽኑ፣ በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መካከል በቅንጅት መሥራት ላይ ክፍተት መኖሩ፣

155. **በኮሚሽኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

- በኦዲቱ ወቅት በትግራይ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል፣ በአዲስ አበባ፣ በአክሱምና ባህርዳር ከተማ ኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በመቀሌ፣ ባህርዳርና አዲስ አበባ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት የሌለ መሆኑና የባህብቱ መረጃዎች በአግባቡ እየተያዙ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ክፍል ሰባት

የማሻሻያ ሐሳቦች

156. **በኮሚሽኑ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከባለሃብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ጥያቄ የቀረቡ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

- *በኮሚሽኑ መውጣት የሚገባቸው የአፈፃፀም መመሪያዎች ሊወጡና ሊተገበሩ እንዲሁም ኢንቨስትመንት ለመደገፍ የተቋቋሙ የወጡ አዋጆችና ደንቦች መሰረት በማድረግ ሊሰሩ ይገባል፡፡*
- *ኮሚሽኑ ለባለሀብቶች የሚሰጠው ማበረታቻ ውጤታማ እንዲሆን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲያወጡ የአዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡ ሊያደረግና ያላቸው የፋይናንስና የሰው ኃይል ብቃት ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡*
- *ኮሚሽኑም ሆነ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚሰጡ አካላት ባለሀብቱ ከውጭ የማያመጣቸውን ዕቃዎች ለፕሮጀክቱ ያላቸውን አግባብነት ሊያረጋግጥና በግንባታና ካፒታል ዕቃ ላይ አግባብነቱ ለማረጋገጥ እንዲያስችል ምን ያህል መጠን ማስገባት እንዳለባቸው ስታንዳርድ ሊወጣላቸው ይገባል፡፡*

- ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎችና ተሽከርካሪዎች ደንቡን መሠረት በማድረግ ሊፈቀዱ ይገባል፡፡
- የነፃ ገቢ ግብር አስመልክቶ ሥራው በኃላፊነት መሥራት ያለበት አካል በመመሪያ ግልጽ ሆኖ ሊወጣና ነፃ ገቢ ግብር ያገኙ ባለሀብቶች እንደ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻው በማዕከል የተደራጀ መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡

157. **ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጥር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤**

- ባለሀብቶች የቀረጥ ነፃ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች መጠንና ዓይነት ለመወሰን እንዲያስችል በቅድሚያ የዕቃዎችን ዝርዝር እንዲያቀርቡ ሊደረግና ያንን መሰረት በማድረግ የኢንቨስትመንት ቢሮዎቹ ሊፈቅዱ ይገባል፡፡
- ነባር ባለሀብቶች የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በፊት የነበራቸው አፈጻጸም ሊገመገምና አፈጻጸማቸውን መሰረት በማድረግ ሊፈቀድ ይገባል፡፡
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰጡ አካላት ፕሮጀክቶቹ በትክክል መኖራቸውንና ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ ማንኛውም ባለሀብት ስለኢንቨስትመንቱ የአፈፃፀም ሂደት በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊያደርጉና የቀረጥ ነፃ ማበረታቻው ዓላማ ባለሀብቱን በማበረታት አገሪቷን ወደ ተሻለ ዕድገት ማምጣት እንደመሆኑ የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠት ብቻ ሳይሆን ፕሮጀክቶች በሙሉ ዕቅድ አውጥቶ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸው ላይ ትኩረት ሰጥተውና አቅማቸውን አጠናክረው ሊከታተሉ ይገባል፡፡
- ኢንቨስትመንት ቢሮዎቹ የቀረጥ ማበረታቻ ወስደው ለታለመላቸው አላማ ያዋሉ ባለሀብቶች ሊሰርዙና እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የተሰረዙና የቀረጥ ማበረታቻውን የወሰዱ ባለሀብቶች ዝርዝር ለይተው ሊየሳውቁ፣ እንዲሁም ላልተፈለገ አላማ ወይም ለሦስተኛው ወገን አውለው ሲገኙ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ቀረጥ ከነቅጣቱ እንዲከፍሉ የሚያስችል አስገዳጅ ህግ ሊወጣና ሊተገበር ይገባል፡፡

- ኮሚሽኑ ሥራውን በጥራት በአግባቡ ለመሥራት እንዲያስችለው ከኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንም ሆነ ሌሎች ከሥራው ጋር ግንኙነት ካላቸው አካላት ጋር ጠንካራ የሆነ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የተቀናጀ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ላይ ያሉ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ከባለሀብቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

158. **በኮሚሽኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

- በኮሚሽኑ፣ በኢንቨስትመንት ቢሮዎችና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መረጃዎች በቀላሉ ለማግኘትና /መረጃዎችን online/ በቀላልና በቅልጥፍናና ሥራዎችን በጥራት ለመሥራት የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

አባሪ 1

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሥራ ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ



ለጉምሩክ ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻን የመፍቀድ አገልግሎት የተጠቃለለ የሥራ ፍሰት መግለጫ



የፕሮጀክት ክትትል የሥራ ፍሰት



አባሪ 2

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫና (AUDIT ISSUES) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

(EVALUATIVE CRITERIA)

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (AUDIT ISSUES)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA)
1. በኮሚሽኑ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከባለሃብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ጥያቄ የቀረቡ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤	1.1 ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ በተመለከተ የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን መሠረት በማድረግ፣ መመሪያ ሊያወጣና ሊተገብር ይገባል፡፡
	1.2 የኢንቨስትመንት የንግድ ሥራ ፍቃድ እንዲሰጠው ጥያቄውን ለኮሚሽኑ የሚያቀርብ ባለሀብት የፕሮጀክቱን አዋጭነት ጥናት (feasibility study) ማቅረብ አለበት፡፡
	1.3 ኮሚሽኑ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተጠየቁት መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና አክሰሴሪዎቻቸው ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፣
	1.4 ኮሚሽኑ ለባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከመስጠቱ በፊት ባለሀብቱ ያለው የፋይናንስ አቅምና የሰው ኃይል ሊገመገም ይገባል፡፡
	1.5 ከቀረጥ ነፃም ሆነ ከገቢ ግብር ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆን ማንኛውም ባለሀብት አስፈላጊውን መረጃ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት ቢሮ ወይም የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (AUDIT ISSUES)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA)
	1.6 ኮሚሽኑ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 ላይ እንዲሰጥ ለተፈቀዱ ዘርፎች በአንዱ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅት ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈለጉ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ፍቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡
	1.7 ኮሚሽኑ ለሚሰጣቸው የማበረታቻ አገልግሎቶች ወጥ የሆነ መስፈርት /standard/ ሊኖረው ይገባል፡፡
	1.8 ኮሚሽኑ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል እቃዎች ጠቅላላ ዋጋ 15 በመቶ የማይበልጡ መለዋወጫዎችን ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት አመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ሊፈቅድ ይገባል፡፡
	1.9 ኮሚሽኑ ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጪ እንዲገቡ የሚፈቅደው የተሽከርካሪዎች ዓይነት እና ብዛት በስራ መስክ እና በሚቋቋምበት የልማት አካባቢ ቦርዱ መጋቢት 4 ቀን 2005 ባወጣው መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡
	1.10 የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ባለሀብት በደንብ ቁጥር 270/2005 ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ሊፈቀድለት ይገባል፡፡
	1.11 ማንኛውም ባለሀብት ቢያንስ 60 በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጪ የሚልክ ወይም ወደ ውጪ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ በደንብ ቁጥር 270/2005 ባለው ሰንጠረዥ ከተፈቀደለት በተጨማሪ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ ሊሆን ይገባል፡፡
2. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች	2.1 ኮሚሽኑ ባለሀብቶች አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ሊያደርግ ይገባል፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (AUDIT ISSUES)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA)
ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፤	
	2.2 ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከተው የኢንቨስትመንት አካል በቅድሚያ በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡
	2.3 የነባር ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመፍቀድ ኮሚሽኑ አስቀድሞ የበፊት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት አፈፃፀማቸውን ሊያይ ይገባል፡፡
	2.4 የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ባለሀብት ከገቢ ግብር ነፃ በሆነበት ዘመን የሚያገኘውን ገቢ አግባብ ላለው የገቢ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
	2.5 ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በሙሉ ዕቅድ አውጥቶ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡
	2.6 ኮሚሽኑ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት በማበረታቻነት ያገኛቸውን ጥቅሞች ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች አካላት ተመላሽ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	2.7 በኮሚሽኑ ፍቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች በኮሚሽኑ፣ የተሰጡ ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ውለው ወይም ከህግ ውጪ ለሌላ ሰው ተላልፈው ከተገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊሰርዝ ይገባል፡፡
	2.8 በኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ባለሀብት ስለኢንቨስትመንቱ የአፈፃፀም ሂደት በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊያደርግ

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (AUDIT ISSUES)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA)
	ይገባል፡፡
	2.9 ኮሚሽኑ ቦርድና የሥራ አመራሮች መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት /የስራ አመራር/ የውይይት መድረክ ሊኖራቸው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉባኤ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡
	2.10 ኮሚሽኑ በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር /የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ሚኒስቴር፣ የክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ …. / ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር በማመቻቸት በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡
	2.11 ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ከባለሀብቶች ጋር በኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ የመወያያ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
3. **ኮሚሽኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፤**	3.1 የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆኑ ባለሀብቶች መረጃ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ በየደረጃው ተለይተውና ተደራጅተው በአግባቡ ሊቀመጡ ይገባል፡፡
	3.2 ኮሚሽኑ ከክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ከባለድርሻ አካላትና ከባለሀብቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት (ድረ-ገጽ፣ ኢ-ሜይል፣ …) ሊዘረጋና (ዕቅዶች፣ሪፖርቶች፣ መመሪያዎችና የመሳሰሉት) በወቅቱ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	3.3 ኮሚሽኑ አገልግሎቱን በቅልጥፍናና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡
	3.4 ኮሚሽኑ ባዘጋጀው እስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡